## 2.3. የሐዋርያው ጳውሎስ ትምህርት፥

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለቤተሰቦችና ስለ ጋብቻ ጉዳዮች በስፋት ሲገለፅ የምናየ ው ሐዋርያው ጳውሎስ ስለሆነ፤ ትምህርቱን የገለፀባቸው ክፍሎች ማለትም 1ቆሮን ቶስ ምዕራፍ ሰባትን፤ 1ጢሞቴዎስንና፤ የኤፌሶንን መጽሐፍ በመጠኑ እንዳስሳለን::

**1) የባልና የሚስት ግዴታ፥** (1**ቆሮ**. 7፡ 2-5)

በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ የተጠቀሰው *"ስለጻፋችሁልኝስ ነገር ከሴት ጋር አለመገናኘት ለሰው መልካም ነው::"* (ቁ. 1) የሚለውን ሐሳብ እንመልከት:: የቆሮንቶስ ሰዎች በተለያዩ አሳሳቢ ጉዳዮች ላይ ያተኰረ ደብዳቤ ለሐዋርያው ጳውለ -ስ ፅፈውለት እንደነበረ እንረዳለን:: ጳውሎስ በዘመኑ የነበረውን ግላዊ መመፃደቅ የሞላበትና "ከማግባት ይልቅ ሳያገቡ መኖር የበለጠ መንፈሳዊነት ነው" ብሎ የሚ ያምን የነበረውን የሐሰት ትምህርት (asceticism) ላይ የፀናና ይህን ትምህርት የሚ ፃረር አቋም እንደነበረው በግልፅ ያሳያል:: (1ቆሮ. 7፡ 1-2) በዘመኑ የነበረው ትምህ ርት"ሰው ለማግባት ያለውን ሥጋዊ ፍላጎት ጨቁኖ ወይንም ወደ ውስጥ ሰርጉዶ በመንፈሳዊ ዓለም ውስጥ መግባትና ማደግ ይቻላል" ብሎ የሚያስተምር፥ ማግባትን ም የሚቃወምና የሚያናንቅ ትምህርት ነበር:: በተጨማሪም በጋብቻ ዓለም ውስጥ የገቡትን ደግሞ ከግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዲጠበቁ፥ እንዲርቁና "የጠለቀውንና የላ ቀውን መንፈሳዊነት" እንዲከታተሉ ከተቻለም ሚስቶቻቸውን ወይም ባሎቻቸውን እንዲፈቱ የሚያበረታታ ትምህርት ነበር::

ሐዋሪያው ጳውሎስ ግን ምንም እንኳን አለማግባት ለእግዚአብሔር መንግ ሥት ሥራ እንደሚጠቅም ቢያምንበትም፤(1ቆሮ. 7፡ 7-9፥ 25-28፥ 32-35፤ ማቴ. 19፡ 10-12)፤ በጋብቻ መጣመርን ወይም ማግባትን ግን የከበረና የሚያበረታታው ጉዳይ እንደነበረም እናያለን::(1ቆሮ. 7፡ 2-5፤ 10-11፤ 12-16)::

**2) የጋብቻ ክቡርነት፥**

**(1ጢሞ.** 2፡ 15፤ 4፡ 1-4፤ 3፡ 4-5፤ 3፡ 12፤ 5፡ 17)

ሐዋርያው ጳውሎስ ለጋብቻ ያለውን አክብሮት በዘመኑ የነበሩትን የሐሰት አስ ተማሪዎችን *"እነዚህ ውሸተኞች መጋባትን ይከለክላሉ::"* በሚል ኃይለ ቃል ሲያጋል ጣቸው እንመለከታለን:: እንዲያውም እነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች፡- *"...የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያደመጠ*

-...” ይላቸዋል፡፡(4፡ 1) ይልቁንም “*እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ መልካም ነውና፤ ከምስጋና ጋር ቢቀበሉት የሚጣል ምንም የለም፡፡ በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት የተቀደሰ ነውና፡፡*” ይላል፡፡ (4:4) ከዚህ በተጨማሪ ጳውሎስ ለጋብቻ የነበረውን አመለካከት በማጠናከር ሚስቶች ልጆችን በመውለድ ያላቸውን ድርሻ (2:15) ሲነካ፤ ለመጋቢነትም የሚሾሙ ይሁን ለሽምግልና የሚመረጡ የአመራር ችሎታቸው መለካት የሚኖርበት ቤተሰባቸውን የመምራት ችሎታቸው ታይቶ በጥልቀት መመዘን እንዳለበት ያስገነዝባል፡፡ (3፡ 4-5)፤ 5፡ 17፤ ቲቶ 1፡ 6) ዲያቆናትም ለአገልግሎት ከመለየታቸው በፊት የቤታቸውን አመራር በመለካት መሆን እንዳለበት (3፡ 12፤ ቲቶ 1፡ 6) በማስረገጥ ሐሳቡን ሲገልፀው እንመለከታለን፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ የጋብቻ አመሠራረት ያለውን ሥነ መለኮታዊ አመለካከት ፍጥረትና ውድቀትን ሳይገልፅ አላለፈም፡፡(1ጢሞ. 2፡ 13-14)

**3) የባልና የሚስት ድርሻ፥ (ኤፌሶን 5፡ 21-33)**

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለጋብቻ በዝርዝር ፅፎ የምናገኘው በኤፌሶን 5:2-33 ባለው ክፍል ውስጥ ስለሆነ ይህንን ክፍል በሰፊው ዐውድ በመጽሐፉ ዓይን ሆኖ እንመለከተዋለን፡፡ የኤፌሶን መጽሐፍ በሦስት አበይት ሐሳቦች ማጠቃለል ይችላል፡፡

- ❖ በዘላለም ውስጥ የነበረው የእግዚአብሔር ሐሳብ በጊዜው ውስጥ በክርስቶስ በኩል በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መፈጸሙን እኛም በእግዚአብሔር ፀጋ መዳናችንና ከአይሁድና ከአህዛብም ለራሱ ክብር አንድ አዲስ ለሕብረተ ሰብ ማቋቋሙን (ምዕራፍ 1፡ 1-2፥ 13)
- ❖ በልዩነት ውስጥ አንድነት፤ በአንድነትም ውስጥ ልዩነት እንዳለ በማወቅና በመረዳት “የመንፈስን አንድነት” ለመጠበቅ የፍቅር የቅድስናና የይቅርታ ኑሮ መኖር (ምዕራፍ 3:14-5:20)
- ❖ በክርስቶስ አካል ውስጥ የግንኙነት ሥምረት ወሳኝ በመሆኑ ምክንያት በባልና በሚስት መካከል፤ በወላጆችና በልጆች መካከል፤ በሠራተኞችና በአሠሪዎች/ በአለቆች መካከል ያለው ግንኙነት መጽናት እንዳለበትና የቅዱሳን ጠላት የሆነውን ዲያብሎስን ግን በፅናትና በትጋት መቋቋም/ መዋጋት (ምዕራፍ 5:21-6:24) እንዳለባቸው በጥብቅ ያስገነዝባቸዋል፡፡

ስለዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ የጋብቻን ጉዳይ እንድናየው የሚፈልገው የእግዚአብሔር ዓላማ “*...በዘመኑ ፍፃሜ ይደረግ ዘንድ ያለው አሳቡም በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ ለመጠቅለል...*” ስለሆነና በመጨረሻውም ዘመን ዕድሳት

ከሚያስፈልጋቸው ዋነኛ ጉዳዮች አንዱ እንደሆነ ነው። በሌላ በኩል ሙሽራ ሆኖ ሊገለጥ ባለው በጌታ በኢየሱስና ሙሽራይቱ ሆና መዘጋጀት ባለበት በቤተ ክርስቲያን መካከል የግንኙነት ሥምረት እንደሚያስፈልግ ሁሉ፤ በባልና በሚስት፥ በወላጆችና በልጆችም መካከል ያለው የግንኙነት ሥምረት መታደስ አለበት። ክርስቶስም የቤተ ክርስቲያን ራስ መሆኑን የገለፀውና አመራሩን ያሳየው በፍቅርና ሕይወቱን መስዋዕት አድርጎ በመስጠት ስለሆነ ባሎችም እንዲሁ ለሚስቶቻቸው ሊያደርጉ ቤተ ክርስቲያንም ጌታዋንና አምላኳን በመታዘዝ ፍቅርንና አክብሮቷን እንደምትገልፅ እንዲሁ ሚስቶችም ለባሎቻቸው ሊያደርጉ ይገባቸዋል። (ኤፌ. 5፡ 21-33)

ሐዋርያው ጳውሎስ በምዕራፍ 1-2 እንደገለፀው እግዚአብሔር *"ሁሉንም በክርስቶስ ለመጠቅለል"* ካለው ዓላማ የተነሣ በአይሁድና በአህዛብ መካከል ያለውን የጥል ግድግዳ እንዳፈረሰው ከሁለቱም አንድ አዲስ ሕብረተ ሰብ እንዳስነሣ፤ በእምነታችንና በአገልግሎት ስጦታችን መሃልም አንድነትም ልዩነትም እንዳለ መገንዘቡ እጅግ አስፈላጊ ነው ብዬ አምናለሁ። በአንድ በኩል አንድነት እንዳለ እናያለን፥ "በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደተጠራችሁ፥ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤ አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት፤ ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ።" (ኤፌሶን 4፥ 4-6) በሌላ በኩል ደግሞ ልዩነትም እንዳለና የአንድነት የውስጥ ውበት የሚገልፀው በልዩነት ውስጥ እንደሆነም ልንገነዘብ እንችላለን፥ "ነገር ግን እንደ ክርስቶስ ስጦታ መጠን ለእያንዳንዳችን ጸጋ ተሰጠን። ... እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋያርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፥ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ።" (ኤፌሶን 4፥ 7-11)

እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎች በሚሰጥበት ጊዜ ለክርስቶስ አካል ሲል ስለሆነ፤ የጸጋ ስጦታውን ስንጠቀም አካሉን ለማነጽ ሊሆን ይገባዋል። እንደዚሁም ክርስቶስም የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደሆነና ቤተክርስቲያንም ለዚህ ጌታ በመስጠትና በመገዛት መኖር እንዳለባት ሁሉ፤ በጋብቻም ውስጥ እንደዚሁ መንፈሳዊ ዕድሳት ሊኖር ይገባል። ከዚህም ሌላ ምዕመናን/ አማኞች የክርስቶስን ፍቅር በመጠበቅ የቅዱሳን አንድነት መጠበቅ እንዳለባቸው ካሳሰባቸው በኋላ (4፡ 1-3፤ 5፡ 1-2)፥ በአንፃሩም ከዝሙት (Porneoia=Sexual Immorality) እንዲጠበቁና (5:3-14)፤ ይልቁንም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በየጊዜው እንዲሞሉ ይመክራቸዋል፤ ያበረታታቸዋልም። በዘመን ፍፃሜ እግዚአብሔር የመሠረተው ሕብረተ ሰብ

እንዲህ ሊሆን ስለሚገባ፣ በጋብቻ በተጣመሩ ባልና ሚስት መካከልም ለዚህ ዓይነት ኛ መሣሪያ በመሆናቸው እንዲህ እንዲሆኑ ይጠበቅባቸዋል።

የሐዋርያው ጳውሎስ የኤፌሶን መጽሐፍ ትምህርት በሚከተሉት አሳቦች ማጠቃለል እንችላለን።

- አንደኛ፥ የክርስቲያን ጋብቻ መታየት ያለበት እግዚአብሔር በመሠረተው ከአይሁድና ከአሕዛብ መካከል በእምነትና በጸጋ የጸነ አዲስ ሕብረተ ሰብ ካደረገው እድሳትአንፃር ነው።
- ሁለተኛ፥ ጳውሎስ "ሚስቶች ደግሞ በሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ" በሚልበት ጊዜ (5፡ 23-25) በአንድ በኩል "መገዛት" (Submission) ከሚስት ብቻ ሳይሆን፥ ከሁለቱም ማለትም፥ ከባልና ከሚስት የሚጠበቅ (mutual submission) መሆኑንና፣ ባሎች ደግሞ ለሚስቶቻቸው ፍቅር የተሞላበት አመራር እያሳዩ የመስዋዕትነት ኑሮ መኖር እንደሚገባቸው ነው። ጳውሎስ "ባል የሚስት ራስ ነውና" የሚለው አባባሉ (5፡ 23)የሚያሳየው ባል የአመራር ሚና እንዳለው ሲሆን፣ ይህንን ሚናውን የሚለማመደው ግን ፍቅር በተሞላ አመራር ነው። አስቀድሞ የተፈጠረውና የአመራር ኃላፊነትም ከእግዚአብሔር የተቀበለው ወንድ ነው። (ዘፍ. 2:7፣ 1ቆሮ. 11:8፣ 1ጢሞ 2:13፣ ዘፍ. 2፡ 15-17)፣ እግዚአብሔር ሴትን ከወንድ ከመፍጠሩም ሌላ (ዘፍ. 2:21-22፣ 1ቆሮ. 11:8-9) የወንድ "ረዳት" እንድትሆን አድርጓታል። ቢሆንም ሴት፥ ወንድ ማየት ያልቻለውን የማሳየት ትልቅ ሚናና ችሎታ አላት። (ዘፍ. 2፡ 18-20)
- ሦስተኛ፥ ጳውሎስ የገለጸው "ራስ" የመሆንና "የመገዛት" ድርሻ ግን እንደ ድርጅታዊ መዋቅር የሚታይና ሚስቶችን የባሎች "ተገዢ/ ባሪያ" እንደሆኑ የሚገልፅ ሳይሆን፣ የፍቅር ቅብብሎሽ የሞላበት የግንኙነት ሥምረት እንደሆነ በሚገባ ያሳያል። ይህ ሁኔታ መታየት ያለበት አንድም እግዚአብሔር ወልድ የሆነው ጌታ ኢየሱስ ለእግዚአብሔር አብ በተገዛበት መገዛትና (ፊል 2:5-11)፣ ሌላውም ደግሞ ይኸው ጌታ የቤተ ክርስቲያን ራስ በመሆን በገለፀው የአገልጋይነት አመራርና፣ ከፍቅር የተነሣ ካሳየው መስዋዕትነት አንፃር መሆን ይገባዋል። (ኤፌሶን 5፡ 23፣ 26-27)

## 2.4 የአዲስ ኪዳን ጋብቻ ገፅታ፥

### 2.4.1 ጋብቻ በወንጌላት እይታ፥

#### 2.4.1.1 የጌታ ኢየሱስ ወላጆች፥ ማርያምና ዮሴፍ:-

(ማቴ. 1፡ 18-23፤ ሉቃስ 1፡ 26-2፡ 52)

ይህ ቤተሰብ ማለትም የኢየሱስ ወላጆች የነበሩት ማርያምና ዮሴፍ በምድር ላይ ከነበሩት ቤተሰቦች በሙሉ በጣም የተለየና እጅግ የጠለቀ ዕጻሎትና ተግጻሮት ም ያጋጠመው ቤተሰብ ነው:: እግዚአብሔር ሰማያዊ መልዕክቱንና ጥሪውን የጌታ ችን እናት ልትሆን ከሴቶች መካከል መመረጧን በመልአኩ ገብርኤል በኩል የተናገ ረው የዮሴፍ እጮኛ በነበረችበት ወቅት ነው:: በአይሁዶች ዘንድ የመተጫጨት ጊዜ ከመጋባት የሚለየው አብረው ለመኖር አለመቻላቸውና እስኪጋቡም ድረስ ንፅህናቸ ውን መጠበቅ ስላለባቸው እንጂ፤ "ቃል ኪዳኑ" ግን በእነርሱ መካከል ብቻ ሳይሆን በሕብረተሰቡም ዓይን የተጠበቀ ነበር:: በዚህ ምክንያት ነው ዮሴፍ ማርያም ማርገዟ ን ባወቀ ጊዜ "በስውር ሊተዋት" አስቦ የነበረው (ማቴ. 1:18-19):: ይህ ሁኔታ በእ ጮኛሞቹ መካከል ከጥርጣሬም ያለፈ መለያየትን፥ ጥላቻንና በቀልን ሊያስከትል ይችል ነበር:: ነገር ግን ማርያምም ሆነ፥ ዮሴፍ የእግዚአብሔርን ድምፅ ለማድመጥ ና ለመታዘዝ በመቻላቸው "ችግሩ" በጋብቻቸው ፕላንም ሆነ ኑሮ ላይ ተጽዕኖ ሲያመጣ አናይም::

የውስጣቸውን ችግር ከፈቱ በኋላ ግን ሌላ ሊወጡት የማይችሉት ከውጭ የሚ መጣው ማዕበል ነበር:: በብሉይ ኪዳን ህግ መሠረት ከሌላ ወንድ ጋር አመንዝራ የተ ገኘች ሴት በድንጋይ ተደብድባ መገደል ነበረባት (ዮሐ. 8:1-11):: ሆኖም ዮሴፍ በቆራጥነት አብሮአት በመቆሙ ምክንያት ይህንንም ኬላ/ ግርዶሽ አለፉት:: ሌላው መጠቀስ ያለበት አብይ ጉዳይ ደግሞ ዮሴፍ ያልወለደውን ልጅ (የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን) "አሳዳጊ አባት" ሆኖ ለማሳደግ ጠንካራ ውሳኔ መወሰን የነበረበት መሆኑን ነው:: ማርያምና ዮሴፍ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነውን፥ የዓለም መድኃኒት የሆነውን ጌታና መሲህ በቤታቸው ቢያንስ ለ30 ዓመታት ለማስ ተናገድ መፍቀድ ትልቅና እጅግ የጠለቀ መሰጠትን የሚጠይቅ ጉዳይ ነው:: ሌላው ደግሞ ምንም እንኳን የኢየሱስ የአገልግሎት ዘመናት (31/2 ዓመታት) ብዙ ህብር የሞላባቸው እጅግ የሚያስደንቅና እስትንፋስን የሚያቆሙ ብዙ ተአምራቶች፥ ድን ቆችና፥ ምልክቶች ሲያደርግ ዝናው ሁሉ በዓለም የወጣበት ዘመናት ናቸው:: በአንጻ ሩ ደግሞ ግን ከልጅነቱ ወራት ጀምሮ ንጉሥ ሄሮድስ ያደረገው የግድያ ሙከራ

(ማቴ. 2:1-18)፥ የእነርሱ ሕጻኑን ይዘው ወደ ግብፅ መሰደድ፥ የፈሪሳውያን የጸሐፍትና የሰዱቃውያን የማያቋርጥ ጥላቻና የግድያ ፕላን፥ የሰይጣን ፈተናና (ማቴ. 4:1-11) ብሎም አይሁድንና ሮማውያንን አስተባብሮ በመስቀል ላይ እንዲገደል ማድረግ፤ እንደ ወላጆች በማርያምና በዮሴፍ ላይ ያለፈው ሰይፍ "*...በአንቺም ደግሞ በነፍስሽ ሰይፍ ያልፋል*" የተባለላትን ስናይ፤ (ሉቃስ 2:35) የመከራቸው ብዛትና የእሣት ወላፈን ማን ሊመጥነው ይችላል?!! (ማቴ. 27:24-54፤ ማር. 15:1-39፤ ሉቃስ 23:1-49፤ ዮሐ. 19:26-27)

ሌላው የስሜታቸው ደረጃ ከወደቀበት ለመነሳት ኢየሱስ የእነሱና የሕዝቡም ሁሉ አዳኝ መሆኑ የታየበት የትንሳኤ የኃይል፤ በትንሳኤ አካሉ እየተመላለሰ ለአርባ ቀን የእግዚአብሔርን መንግሥት እያስተማረ መቆየትና የምድር ስበት ሳይዘው ወደሰማይ ማረግ የሚገርም የእምነትና የልምምድ ሽግግር በእነሱ ላይ ማምጣቱ የማያጠራጥር እውነት ነው:: በመጨረሻም ይህ ቤተሰብ (ዮሴፍም እንደነበረ በመገመት) ጌታ ኢየሱስ "*ሌላ አፅናኝ (Another of the Same Kind) ይሰጣችኋል*" እንዳለው፤ መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያትና በሌሎቹ ላይ ሲወርድ ማርያም በዚያው መገኘቷን ስንመለከት (የሐዋርያት ሥራ 1:12-14፤ 2:1-4) ይህ ልምምድ ለማርያም ምን ያህል የጠለቀ ዕጻሎትና ተግዳሮት እንደሚያመጣ መገመት የሚያዳግተን አይሆንም::

**2.4.1.2 የመጥምቁ ዮሐንስ ወላጆች:- ዘካርያስና ኤልሳቤጥ:- (ሉቃስ 1:5-25)**

ዘካርያስ በእግዚአብሔር ቤተ-መቅደስ ካህን ስለነበርና "*ሚስቱም ከአሮን ልጆች ነበረች...*" ስለሚል (ሉቃስ 1:5) ሁለቱም የአሮን ወገን እንደነበሩ ማየት እንችላለን:: ዘካርያስና ኤልሳቤጥ የውስጥና የውጭ ጫና የነበረባቸው ቤተሰብ ቢሆኑም፤ በጣም ወሳኝና ቀውጢ በሆነ ዘመን ውስጥ፥ ማለትምበብሉይና በአዲስ ኪዳን ዘመናት መሸጋገሪያ በሁለት የታሪክ መጋጠሚያ ላይ የነበሩ ቤተሰብ ናቸው:: ሁለቱም ያጋጠማቸው የውስጥ ጫና ለመውለድ አለመቻላቸው ብቻ ሳይሆን፥ በዕድሜአቸው እያረጁ መምጣታቸው ነው:: በአንፃሩም የውጭ ጫናም ነበረባቸው፤ አንድም ይኖሩበት የነበረው ዘመን "*በይሁዳ ንጉሥ በሄሮድስ ዘመን*"(ሉቃስ 1: 5) ስለነበረ፤ ንጉሥ ሄሮድስ ደግሞ በቤተልሔምና በአውራጃዋም ከሁለትዓመት በታች የነበሩትን ህፃናትን ያስገደለና "ብዙ ልቅሶና ዋይታም" በራማ እንዲሰማ ያደረገበት የጭንቅ ዘመን ነበር::

ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ግን ይህንን ሁሉ ተግዳሮት አልፈው **የማያቋርጥ የቅድስና ሕይወት** (ሉቃስ 1:6)፥ **የማያቋርጥ የአገልግሎት መሰጠትና**፥ (ሉቃስ 1:8-11)፤ **የማ**

ያቋርጥ የጸሎት ሕይወት (ሉቃስ 1:13÷24-25) የነበራቸው ቤተሰብ ነበሩ:: እንዲህ ዓይነቱ የመስጠት ሕይወታቸው ለእግዚአብሔር የተመቸ ስለነበር በነቢዩ በኢሳያስ ምዕራፍ 40:3-5 የእግዚአብሔር ልጅ የሆነውን አዳኝ/ መሲህ መምጣቱን የሚያበስርና÷ የሰዎችን ልብ በማዘጋጀት መንገድም የሚጠርግለትን መጥምቁ ዮሐንስን ለመውለድ ምክንያት ሆነው እናያቸዋለን:: (ሉቃስ 1:15-17) በተጨማሪም ዘካሪያስና ኤልሳቤጥ በእርጅናቸው ወራት የወለዱት ዮሐንስ እጅግ ብርቅ ሊሆንባቸው ቢገባም ÷ ሊመጣ ላለው አዳኝና መሲህ የነበራቸው አክብሮትና ያሳዩት ትህትና እጅግ የሚያስደንቅ ከመሆኑም በላይ፤ (ሉቃስ 1:39-45፤67-79) ይኸው የትህትና መንፈስ ልጃቸው በሆነው በመጥምቁ ዮሐንስም ያለምንም መለወጥ ሲንፀባረቅ እናያለን:: (ዮሐንስ 1:29-34፤3:25-30)

በአንፃሩም መጥምቁ ዮሐንስ በተነበየው ትንቢት ሄሮድስን ስለገሰፀው በእስር ቤት ተጥሎ በነበረበት ቀውጢና ወሳኝ በሆነ ወቅት *"የሚመጣው አንተ ነህን ወይስ ሌላውን እንጠብቅ?'* ብሎ ሁለቱን ደቀመዛሙርት መላኩን ስናይ፤ (ሉቃስ 7:18-19 ፤ ማቴ. 11: 2-3)፤ አባቱ ዘካርያስ ወሳኝ በሆነ ወቅት መልአኩ ገብርኤል *"ወንድ ልጅ ትወልዳለህ... ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ'* ባለው ጊዜ ከእምነት ጉድለት የተነሣ *"እኔ ሽማግሌ ነኝ ሚስቴም በዕድሜዋ አርጅታለችና ይህን በምን አውቃለሁ?'* ብሎ ከጠየቀው ጥያቄ ጋር የሚጣጣም (corrolate) መሆኑን ልንገነዘብ እንችላለን:: በአጠቃላይ ግን ይህ ቤተሰብ በመልካም ምሥክርነታቸውና የመሲሁን መንገድ የጠረገ/ ያዘጋጀ በብሉይና በአዲስ ኪዳን ዘመን መሸጋገሪያ ላይ የተነሣ ነቢይ በመውለዳቸው የተባረኩና ለብዙ ሕዝብም የበረከት ምንጭ እንደሆኑ መግለፅ አስፈላጊ ነው:: (ሉቃስ 1: 14-15፤ ኢሳ 40: 3-5)

### 2.4.1 ጋብቻ በሐዋርያት ሥራ እይታ:-

#### 2.4.1.1 የሐናንያና ሰጲራ ቤተሰብ:- (የሐዋ ሥራ 5: 1-11)

መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ ከወረደ በኋላ የመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተች አጭር ወራት ቢሆንም÷ እግዚአብሔር ግን በሐዋርያት እጅ ታላላቅ ነገሮችን የሚያደርግበት፤ ያመኑትም በአንድ ልብ የቆሙበት፤ በውጭ ያሉት ያላመኑት ሕዝብ ደግሞ በታላቅ ፍርሃትና መገረም የተሞሉበት ወቅት ነበር:: እንዲህ ባለ ጊዜ ግን የሐናንያና የሰጲራ ቤተሰብ እግዚአብሔር ያዘጋጀውን የመታደስን ዘመን ለመቀበል ያቃተው የዘመመ ቤተሰብ (dysfunctional family) እንደነበረ እናያለን:: ስለዚህም ለመልካም ነገር ሳይሆን÷ ለክፉ ሲመካከሩና ውሣኔ ሲወስኑ ስናይ

የእግዚአብሔር ቃል "*የሰው ልብ ክፉ ነው፤ ማንስ ያውቀዋል?*" እንዳለው የልባቸው ጥንካሬና መንፈስ ቅዱስንም ለማታለል በመምከራቸው የሞትን ጽዋ እንዲጎነጩ ሲገደዱ እንመለከታለን።


**2.4.1.2 የአቂላና ጵርስቅላ ቤተሰብ፦ (የሐዋ. ሥራ 18፡ 1-28)**

ሐዋርያው ጳውሎስ "*በክርስቶስ ኢየሱስ አብረውኝ ለሚሠሩ*" የሚላቸውና፥ (ሮሜ. 16:3) "*እነርሱም ስለነፍሴ ነፍሳቸውን ለሞት አቀረቡ*" የሚላቸው አቂላና ጵርስቅላ (ሮሜ. 16:4) በአሕዛብ አብያተ-ክርስቲያናትም ዘንድ የተወደዱና የተመሰገኑ ነበሩ። (ሮሜ 16:4) በተጨማሪም ቤታቸውንና ልባቸውን ከፍተው በቤታቸው የቤተ ክርስትያን አምልኮ እንዲካሄድ የፈቀዱ ናቸው። (ሮሜ. 16:5) አቂላና ጵርስቅላም በሮም ውስጥ ከነበራቸው አገልግሎት በእምነታቸው ምክንያት በቀላውዲዮስ ትዕዛዝ ተሰድደው ወደ ቆሮንቶስ መጡ። (የሐዋ. ሥራ 18:1-2) በዚያም ሐዋርያው ጳውሎስን ባገኙት ጊዜ ከእነርሱ ጋር እንዲቀመጥ ከማድረጋቸውም በላይ አገልግሎቱንም በመደገፍ አብረውት ቆመዋል። (የሐዋ. ሥራ 18፡ 3-4) ሐዋርያው ጳውሎስ ለአገልግሎት ወደ ኤፌሶን በተጓዘበት ጊዜ አብረውት ሄደው ነበር (የሐዋ. ሥራ 18:18-19) እንዲያውም በኤፌሶንም እንዲቆዩ ሲወክላቸው እንመለከታለን። (የሐዋ. ሥራ 18:19) በመጨረሻም ጳውሎስ በሮም አገዛዝ ንጉሥ በነበረው በኔሮ እጅ በሮም ታሥሮ ለመገደል ጥቂት ቀናት በቀረውም ጊዜ በጢሞቲዎስ በኩል ሰላምታ ይፅፍላቸዋል። (1ጢሞ. 4፡ 19) ይህ ጊዜ ለጳውሎስ "*ጌታም ከአንበሳ አፍ አዳነኝ፤ ያድነኛማል*" እንዳለው ምንም እንኳን "ብቻውን" ባይሆንም፤ ብዙዎች ጥለውት ስለሸሹ "*በፊተኛው ሙግቴ ማንም አልደረሰልኝም፤ ሁሉም ተዉኝ እንጂ*" ያለበት "በብቸኝነት" የደቀቀበት ወቅት እንደሆነ ስንገነዘብ፤ ለዚህ ቤተሰብ (ማለትም ለአቂላና ጵርስቅላ) የነበረው ፍቅርና አክብሮት ግን በዚህ ቀውጢ ሰዓትም እንኳን አስቦ እንዲፅፍላቸው አስገድዶታል። (2ጢሞ. 4፡ 9-21)

አቂላና ጵርስቅላ የሚታወቁበት ሌላው የሚገርመው ነገራቸው ብዙ ሕዝብ ሲያደንቀውና፥ ምናልባትም ሲያመልከው የምናየውና በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ከነበረው ሕዝብ መካከልም "እኔ ግን የአጵሎስ ነኝ" በሚል የቡድን ስያሜ የሰየሙለትን አጵሎስ (1 ቆሮንቶስ 1፥12) የነበረው የሕይወትና የአገልግሎት ጥራት ጉድለቱን አስተውለው ቤታቸውንና ልባቸውን ከፍተው ከእነርሱ ጋር እንዲኖር ማድረጋቸው ነው። ከዚያም "*የእግዚአብሔርን መንገድ ከፊት ይልቅ በትክክል ገለጡለት። እርሱም ወደ አካይያ ማለፍ በፈቀደ ጊዜ .. አፅናኑት፤ ይቀበሉትም ዘንድ ወደ ደቀ*

*መዝሙርት ፃፉለት። በደረሰም ጊዜ አምነው የነበሩትን በፀጋ እጅግ ይጠቅ ማቸው ነበር።"* (የሐዋርያት ሥራ 18፥ 24-28)

ለማጠቃለል የአቂላና ጵርስቅላ ቤተሰብ በአንድ በኩል እግዚአብሔር ለጠራ ቸውና ለቀባቸው አገልጋዮችም ሆነ፥ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ልዩ ፍቅርና አክብሮት የነበራቸው መሆኑን ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር ከነበራቸው ግንኙነትና በአብያተ ክር ስቲያናት ዘንድ የነበራቸውን መወደድ ስናይ፤ በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር የጠራቸውን አገልጋዮች የግል ጣዖት ለማድረግ የማይፈልጉና፤ ይልቁንም ብዙኃኑ ክርስቲያን ሕዝብ በስሜት ግልቢያ ሲወሰድ፥ እነርሱ ግን ሰክነውና ተረጋግተው በአ ገልጋዮች ውስጥ ያለውን ብርታት ላይ ፀጋን በመጨመር፥ በጎደሉበት ጉዳዮች ደግ ሞ ቤታቸውንና ልባቸውን ከፍተው በማስተናገድ የሚመክሩ፥ የሚቀርፁና፥ መሪዎ ችን የሚያሳድጉ ቤተሰብ መሆናቸውን ከአጵሎስ ጋር ከነበራቸው ግንኙነት መገንዘ ብ እንችላለን። በተጨማሪም የአቂላና ጵርስቅላ ፍቅር የነጠረና የበሰለ ከመሆኑ የተነ ሳ እንደ ፊልሞና (ፊልሞና 1፡1-25) በቤቱ የሚሰበሰበውን የቤተ ክርስቲያን ሕዝብ በጅምላ መውደድ እየቻለ፤ አንዱን የበደለውን ሰው አናሲሞስን ግን መውደድ እንዳ ቃተው ሳይሆን፤ ጫካውን ማየትና መውደድ የሚችሉትን ያህል፥ አንዱንም ዛፍ መንከባከብና ማየት የሚችሉበት ልዩ ችሎታ ነበራቸው።



## 3. የጋብቻና ቤተሰብ ሥነ መለኮታዊ እሳቤ

እላይ በተሰጠው ስዕላዊ መግለጫ የብሉይም ይሁን የአዲስ ኪዳን ሥነ ምግባር (ETHICS) ለመረዳት የሚያስችሉ ዋና መሠረታዊ እውነቶችና መመሪያዎችን ለመ ረዳት እንችላለን፡፡ በቤተሰብ ውስጥ ያለው ግንኙነት ለብዙ ነገር ወሳኝነት አለው:-

- ባልና ሚስት እርስ በርሳቸውም ሆነ፣ ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን ግንኙነ ት እየተበላሸ በመጣ ቁጥር የወለዷቸውን ልጆች ጌታን በመፍራት ማሳደግ ይሳ ናቸዋ ል፡፡ በዚህም ምክኒያት ልጆቻቸውን ብቻ ሳይሆን የሚመጣው ትውልድ ም እንዲዋልል ያደርገዋል፡፡
- ከዚህ የተነሣ ሕብረተ ሰቡ የሞራልና የሥነ ምግባር መለኪያ የሌለው፣ የላሸቀና የተበላሸ ልቅ ትውልድ ይሆናል፡፡ ከጋብቻ በፊትም ሆነ በኋላ ዝሙት፥ መለያየ ትና፥ ፍቺ፣ ከዚያም አልፎ ተመሣሣይ ፆታዎች ጋብቻ፣ በመጨረሻም የጾታዎ ች ድብልቆሽ (TRANSGENDERED) እየበዛ መምጣቱ የማይካድ ሐቅ ነው፡፡
- እግዚአብሔር በቤተሰብም ሆነ በሕብረተሰቡ ያዝናል፣ ይቆጣልም፡፡ ስለዚህም ምድሪቱ ፍሬን እንዳታፈራ፣ ወይንም ፍሬ ብታፈራም የምታፈራው መርዛም እንዲሆን ይረግማታል፡፡
- የመጨርሻው ሰበብ የኢኮኖሚ ድቀት ይሆንና ቤተሰብ ይራባል፣ ሕብረተ ሰቡም በኢኮኖሚ ድቀት ምክኒያት ይታወካል፣ ይጨነቃልም፡፡

❖ <u>በጣም የሚያስደንቀውና ደስ የሚያሰኘው እውነት ግን ቤተሰብን የፈጠረና፥ ቤተሰብም እንዲቆይና፥ እንዲኖር፥ ማድረግ የሚችለው እግዚአብሔር አምላክ ነው፡፡</u>

እግዚአብሔር ጋብቻንና ቤተሰብን በሚመሠርትበት ጊዜ በቃል ኪዳን የተጣ መሩት ባልና ሚስት፣ በኋላ ለሚወልዷቸው ልጆቻቸውና ለሚመጣውም ትውልድ ምሳሌና ሞዴል ሆነው እንዲያስችላቸው አንድነታቸውና ልዩነታቸው በጥንቃቄ ሊገ ነዘ ቡ ያስፈልጋቸዋል፡፡ በመካከላቸው ያለውን ቃል ኪዳን አፅንተው ለመኖር ከፈለ ጉ ሁለቱም "በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ" የተፈጠሩና በእርሱም ፊት እኩል የሆነ በአንድ በኩል ዕዳሎትና ነፃነት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ኃላፊነትና ተጠያቂነት እንዳላቸው ሊያስተውሉ ይገባል፡፡ በአንፃሩም "እግዚአብሔር ወንድና ሴት አድርጎ እንደፈጠራቸውና በየግላቸውም ይሁን፣ ሁለቱም ባላቸው የግንኙነት መሥመር የተ ለያየ ሚና፣ ድርሻና ኃልፊነት እንዳላቸው መገንዘብ አለባቸው፡፡ ከዚህም ሌላ ልጆ

ቻቸውንበማሳደግ፣ በመቅረጽና ለትውልዳቸው የሚበቁ እንዲሆኑ በማድረግ እኩል የሆነ ዕዳሎትና ኃላፊነት፣ ልዩ ልዩ ድርሻም እንዳላቸው መቀበል ይገባቸዋል።

ነገር ግን በባልና በሚስት መካከል፣ በወላጆች እና በልጆቻቸው መካከል የጸጋ መቀባበል ከሌለ ቤተሰቡ የነበረው የኑሮ መመሪያዎች የዋጋ እሴቶች አሰጣጥና የእግዚአብሔር ፍርሃት ከውስጣቸው እየተሟጠጠ መምጣቱን የሚያመለክቱ ገጽታዎች ዓይነተ ብዙ ቢሆኑም፣ ጥቂቶቹን ለመጥቀስ እሞክራለሁ።

<u>አንደኛ</u>፡- እግዚአብሔር ለባሎች በአደራነት ቤተሰባቸውን ለመምራትና ለማስተዳደር የሰጣቸውን የአመራር ኃይልና ሥልጣን ያለ አግባብ የራሳቸውን ክብርና ጥቅም ማስጠበቂያ ሲያደርጉ፣ በሚስቶቻቸው ላይ መንፈሳዊነት የጎደለው ባህርይ ሲያሳዩና ለእግዚአብሔርም ሆነ ለሚስቶቻቸው ያላቸውን ተጠያቂነት ሲረሱ፣ ራሳቸውን ለጌታ በማስገዛትና ሚስቶቻቸውንም ገደብ በሌለው ፍቅር መውደዳቸው ዋና መሠረት መሆኑን ለመገንዘብ ሲያቅታቸው፣ ልጆቻቸውንም በፍቅር፣ በትዕግሥትና በፅናት ከማሳደግና ዲሲፕልን ከማድረግ ይልቅ፣ የአባትነት ትዕቢታቸው ስለተነካብቻ ቅጥ በሌለው ቁጣና መራራ በሆነ ስድብ ሲቀጡ፣ ትውልዳቸውም ለምሬት እንዲሞላ ሲያደርጉ፣ ቤተሰባቸውንም በመጣል በሥራ፣ በስብሰባ፣ ወይም በአገልግሎት እያሳበቡ በዚህ አዙሪት ተጠምደው ከቤት መጥፋት ሲጀምሩ፣

<u>ሁለተኛ</u>፡- ሚስቶች ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው "የረዳትነት አደራ" ማለትም፣ ባሎቻቸው ያላዩትን እንዲያዩ፣ ያላስተዋሉትን እንዲያስተውሉ የሚያደርግ የማስተዋል እና በጥበብ የመምከር ጸጋ መለማመድ ሲያቅታቸው፣ ሚስቶች ለጌታ በመገዛታቸው ለባሎቻቸው በመገዛትና በማክበር ለባሎቻቸው የተሰጠውን የአመራር ኃይልና ሥልጣን እንዲጎለብት ከማድረግ ይልቅ፣ አክብሮት በማሳጣትና ባሎቻቸውንም በመናቅ ሲመላለሱ፣ በባሎቻቸውም ላይ እልካቸውን በመወጣት በእነርሱም ላይ ሲሰለጥኑ፣ የእናትነት ደብዛቸውን እያጠፉ ልጆቻቸውን በጥበብና በማስተዋል ከማሳደግና ትውልዳቸውን ከመቅረፅ ይልቅ ገንዘብን ለማሳደድ ነፍሳቸው ስትወጠር፣ "ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፣ በሚስቱም ይጣበቃል፣ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።" (ዘፍ. 2፡24፣ ማቴ. 19፡5) የሚለውን ቃል ዘንግተው፣ ከባሎቻቸው ይልቅ ከወላጆቻቸው ጋር ተጣብቀው ሲቀሩ፣

<u>ሦስተኛ</u> ወላጆች በጌታ ፍርሃት፣ በጥበብና በመሰጠት፣ በፍቅርና ብንፅህና ለልጆቻቸው ምሳሌ ሆነው ከመኖር ይልቅ፣ በእነርሱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያመጣ ኑሮ ሲኖሩ፣ ልጆቻቸውን ዲሲፕልን በማድረግ ጉዳይ ተቃራኒ የዋጋ አሰጣጥና አቅርቦት

ሲኖራቸው፤ በባልና በሚስት መካከል ያለው ግጭት እየናረ ሲመጣና እርስ በርሳቸው በእርጋታ ተነጋግረው ችግሮቻቸውን ለመፍታት ሲሳናቸው፤ ከዚህ የተነሣ ልጆቻቸው በወላጆቻቸው መካከል የተነሣው ችግር በእነርሱ ምክኒያት እንደሆነ በማሰብ ለህሊና ወቀሳ ሲዳረጉ፤ በራሳቸው ተስፋ በመቁረጥም በወላጆቻቸው ላይ ትከሻቸውን ሲያነሱ፤ ለከፋም ባህርያትና ልምዶች አልፈው ሲሰጡ፤


ቤተሰቡ መፈራረስ (DYSFUNCTIONAL) ከመጀመሩም ሌላ፥ እግዚአብሔር በቤተሰቡ ላይ የነበረው ዓላማ እየደበዘዘ እንዲመጣ ያደርገዋል። ከዚህም ሌላ ልጆቻቸውና ትውልዳቸውም የሞራልና የሥነ መግባር መለኪያ የሌለው፤ ግራ የተጋባና የማይጨበጥ ትውልድ እንዲሆን ያስገድደዋል።

❖ <u>ስለዚህ አንድ ቤተሰብ እግዚአብሔርን በመፍራትና በጽድቅ እንዲኖር ካስፈለገ በባል፤ በሚስትና በልጆቻቸው መሃል አንድነታቸውን በልዩነታቸው ውስጥ በመቀበል፤ ለጌታ በሚገዙበት መንፈስ አንዱ ለሌላው እየተገዛ</u>፤ "*<u>በአንድ ልብ ሆነው በአንድ አፍ</u> እግዚአብሔርን ...ያከብሩ ዘንድ....እርስ በርሳቸው <u>በአንድ አሳብ</u> መሆን...*" (ሮሜ. 15፡ 5-6) ይኖርባቸዋል።

## መ. የቤተሰብ መዋቅር፤ ወይንስ ገደብ የሌለው ፍቅርና የጸጋ ቅብብሎሽ?


1. የሥልጣን መዋቅር ያለው ቤተሰብ፡-

(THE HIERARCHICAL MODEL)





2. አባት ለብቻው የበላይ የሆነበት ቤተሰብ፡-

(THE MONARCHICAL MODEL)




3. አባትና እናት በልጆች ላይ ሥልጣናቸውን የሚገልፁበት ቤተሰብ፡-
(THE FILIOQUE MODEL)





4. በአንድ ልብና በአንድ ሐሳብ የሚፈስ ቤተሰብ፡-
(THE SYMMETRICAL MODEL)


4.1



4.2




4.3




11

---

118 ኃይልስ በነባራዊነቱ ይኸንን መግለጫ የተጠቀመው ስለ ሥላሴ ለመግለፅ ነው:: Kevin Giles, *The Trinity and Subordinationism - The Doctrine of God and The*

ይህንን ክፍል ለማጠቃለል አንድ ቤተሰብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ የቤተሰብ ኑሮ ለመኖር ከፈለገ የሚከተሉትን አራት ነገሮች የግንኙነት መሥመሩን ሊያዳብሩ ለት ይችላሉ::[119] (1) <u>መሰጠት</u> መመሥረት ያለበት ገደብ በሌለው ፍቅርና በመከባበ ር ላይ የቆመ ቃል ኪዳን፤ (2) የቤተሰቡ ሕይወት መሠራትና መጠበቅ ያለበት <u>ጸጋ በተሞላበት መቀባበልና እርስ በርስ ይቅር መባባል</u> በሰፈነበት ሁኔታ፤ (3) ቤተሰቡ ያሉት <u>ምንጮች</u> አንዱ ሌላውን ለማጎልበት ለማድረግ እንጂ፤ ለመቆጣጠር ለማድረ ግ ያልሆነ፤ እና (4) <u>የግንኙነት ሥምረት / ጥምረት መመሥረት</u> ያለበት አንዱ ሌላ ውን በማወቅ መደገፍ፥ መረዳት፥ መቀባበል፥ እና ልባዊ ሕብረት የሚወስድ ሊሆን ይገባዋል::

ረ. መደምደሚያ:-

የጋብቻና የቤተሰብ ሥነ መለኮት እንደተመለከትነው በባል ፤ በሚስትና በልጆ ቻቸው መሃል ያለው ገደብ የሌለው ፍቅርና የጸጋ መቀባበል፤ ትዕግሥትና ጽናት፤ እና ምሕረትና ይቅርታ ቤተሰቡን ጤናማ የሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ኑሮ እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል:: ይህ የጋብቻና የቤተሰብ ሥነ መለኮት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላለ ን የአመራር ሥነ መለኮት መሠረትና ሞዴል ከሆኑት ከሦስቱ የሥነ መለኮት እሳ ቤዎች አንዱ አድርገን መውሰዳችን በጣም ወሳኝ ነው:: <u>በባልና በሚስት፤ በወላጆች ና በልጆች መካከል አንድነት በልዩነት ውስጥ፤ ልዩነትም በአንድነት ውስጥ መገለፅ ያለበትን ያህል፤ በአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንም በፓስተር፤ በቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችና በቤተ ክርስቲያኒቱ ምዕመን መካከል የጸጋ መቀባበልና አክብሮት ሊኖር ይገባል::</u>

---

*Contemporary Gender Debate*. Downers Grove, IL.: Intervarsity Press, 2002.

[119] Jack O. Balswick & Judith K. Balswick, *The Family: A Christian Perspective on the Contemporary Home,* 2nd. ed., (Grand Rapids, MI: Baker Books, 1989, 1999), 33.

## II. የክርስቶስ አካል ሥነ መለኮት

- "*በአንድ አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉን፣ የብልቶቹም ሁሉ ሥራ አንድ እንዳ ይደለ፣ እንዲሁ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን፣ እርስ በርሳችን ም እያንዳንዳችን የሌላው ብልቶች ነን:: እንደ ተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን::...*" (ሮሜ. 12:4-6)
- "*እናንተም የክርስቶስ አካል ናችሁ፣ እያንዳንዳችሁም ብልቶች ናችሁ::*" (1ቆሮ. 12:27)

### ሀ. መግቢያ:-

የክርስቶስ አካል ስለሆነችው ስለ ቤተ ክርስቲያን በምናጠናበት ጊዜ የተለያየ አቅርቦት እንዳለ መረዳቱ ይጠቅማል:: አንደኛው ለረዥም ዓመታት የተጠናከሩ በቤ ተ ክርስቲያን ባህላዊ ታሪክ ላይ የተመሠረቱ አቀራረቦች በቤተ እምነቶች ማለትም ÷ በምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን÷ በምዕራብ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን÷ በሉ ትራን ቤተ ክርስቲያንና÷ በሪፎርምድ ቤተ ክርስቲያን÷ የተሰጡ አቅርቦቶች አሉ:: ሁለተኛው "ነፃ አብያተ ክርስቲያናት" (Free Churches) በመባል የሚታወቁት ወደ ባፕቲስትነት፣ ከዚያም አልፎ ወደ አና ባፕቲስትነት የሚያደሉ ከሪፎርሜሽን ዘመን ጀምሮ የተጀመሩ የፔንትኮስታልና የካሪዝማቲክ ሙቭመንት ስለ ቤተ ክርስቲያን የተሰጠ አቅርቦት አለ::

ሦስተኛው በሲስተማቲክ ቲዮሎጂ ዓለም ውስጥ የተነሱ ብዙ እውቅና ያላቸው የሥነ መለኮት ምሁራን የተሰጡ አቅርቦቶች አሉ:: ለምሳሌ:- ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጆን ዚዚዮላስ፣ ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን:- ሀንስ ኩንግ፣ እና ጆሴፍ ራዚ ንገር በኋላ (ፖፕ በነዲክት አሥራ ስድስተኛው)፣ ከሉተራን ቤተ ክርስቲያን ዎልፍሀ ርት ፓነንበርግ፣ ከሪፎርምድ ቤተ ክርስቲያን ጀርገን ሞልትማን፣ ከኢኩሜኒካል አብያተ ክርስቲያን:- ሚሮስላቭ ቮልፍ ከፔንትኮስታልና ከሪፎርምድ መሠረት/ ዱራያለው፣ ከባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን:- ጀምስ ማክ ክሌንዶን፣ እና ከአንግሊካን:- ሌስሊ ኒውብግን:: አራተኛውና የመጨረሻው አቅርቦት ቤተ ክርስቲያን ካለችበት ዘመንና ዓውድ ላይ የተመሠረቱ የሴቶች መብት አስጠባቂ ድረጅት፣ በላቲን አሜሪ

ካ የበቀለው ሊብሬሽን ቲዮሎጂ፣ እና በአፍሪካ ውስጥ የተነሡት የጥቁሮች ሥነ መለ ኰት እና ኢንዲፐንደንት ቸርችስ (Independent Church) ስለ ቤተ ክርስቲያን የተሰ ጡ አቅርቦቶች አሉ::[120]

እነዚህን ሁሉ በስፋትና በጥልቀት ለማየት ባንችልም በመጠኑም ቢሆን አንዳን ዶቹን ማየታችን የክርስቶስ አካል ምንድን ነው? ቤተ ክርስቲያን ምንድን ነች? በቤተ ክርስቲያንና በክርስቶስ አካል ያለው ግንኙነት ምንድን ነው? የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን እንዴት መመራት አለባት? በቤተ ክርስቲያን ካሉት መሪ ዎች መታየት ያለባቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባሕርያት ምንድን ናቸው? "የሚሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ይረዱናል ብዬ አምናለሁ::

## ሀ. ስለ "ቤተ ክርስቲያን" የቤተ እምነቶች አመለካከት:-

### 1. የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን:-

በክርስትና እምነት ውስጥ ካሉት ቤተ እምነቶች መካከል በሕዝብ ብዛት፣ በቤተ ክርስቲያን መዋቅርና በንብረት አያያዝ ትልቁ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ናት:: የካ ቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ስለ "ቤተ ክርስቲያን" ያላት ሥነ መለኰት በተለያዩ ደረጃዎ ችልንገልፀው እንችላለን:: በመጀመሪያ "ቫቲካን አንደኛ" በ 1871 ዓ.ም. (እ.አ.ዘ.አ .) በተደረገው ውሳኔ ቤተ ክርስቲያንን በመዋቅርና በሥልጣን አደረጃጀት በሚያሳይ

---

[120] John D. Zizioulas, *Being As Communion; Studies In Personhood and the Church,* (Crestwood, N.Y.: St. Vladimir's Seminary Press, 1985); Joseph Ratzinger, *Auf Christus Achauen: Einubung in Glaube, Hoffnung, Liebe, Freiburg, 1989;* Hans Kung, *Die Kirche,* (Munich, Germany: Piper, 1977); Wolfhart Pannenberg, *Anthropologie in Theologischer Perspektive,* (Gottingen: Vandenhoeck & Ruprecht, 1983); Jurgen Moltmann, *The Church in the Power of the Spirit: A Contribution to Messianic Ecclesiology,* (New Yor: Harper & Row, 1977); Miroslav Volf, *After Our Likeness - The Church as The Image of the Trinity*, (Grand Rapids, MI: Eerdmans Publishing Company, 1998); James McClendon, *Doctrine: Systematic Theology,* vol. 2, (Nashville, TN: Abingdon, 1994); Lesslie Newbigin, *"The Logic of Mission," in New Directions in Mission and Evangelization,* ed. James A. Scherer and Stephen B. Bevans, (Mary Knol, N.Y.: Orbis, 1992): 16-25; Newbigin, *The Household of God: Lectures on the Nature of the Church*, (London: SCM Press, 1953); Leonardo Boff, *Trinity and Society,* trans. Paul Burns, (Mary Knoll, N.Y.: Orbis Books, 1998); Desmond Tutu, *"Whither African Theology?"* to Edward Fashole-Luke et.al. (eds.), *Christianity in Independent Africa*, (London: Rex Collings, 1978); John S. Mbiti, *African Religions and Philosophy,* 2nd. ed., (London: Heinemann, 1989); Bolaji Idowu, *African Traditional Religion - A Definition*, (London: SCM Press, 1973).

መልኩ ሲገልስፃት (Hierarchical View)፣ ካውንስሉ በዚህ ጊዜ ነው የፖፑ ስህተት የሌለው መሆኑን ያብራራው:: ፖፑ በሞራልና በሃይማኖት ጉዳይ ምንም ዓይነት ስህ ተትና ግድፈት የሌለው ስለሆነ፣ የሚናገረው ነገር ሁሉ ለዓለም አቀፍ ቤተ ክርስቲያ ን የሚሆን ትዕዛዝ ነው:: ይህ አመለካከት ቤተ ክርስቲያንን የክርስቶስ ቀጣይነት ያለው "አምላክ ሰው የሆነበት መገኘት" አድርጎ ይወስዳታል:: ሁለተኛ ቤተ ክርስቲ ያንን "ምስጢራዊ ሕብረት" የሚወስድ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አቋም ነው:: ይህ አመለካከት በመጀመሪያ ያመነጨው የቀድሞ የቤተ ክርስቲያን አባት የነበረው ቅዱ ስ አጎስቲን ነው:: ለቅዱስ አጎስቲን "የክርስቶስ አካል" እና "ምሥጢራዊ አካል"የሚ ሉት ሐሳቦች አንድ ናቸው::[121] የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የቅዱስ አጎስቲን ሐሳብ ውስጥ ነው የቤተ ክርስቲያን ምንነት የገለፀችበት:: ይህን ያደረገችበት ምክኒያት የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ከነበሩት ምሁራን መካከል ዲያትርች ኖንሆፌር "የቅዱሳን ሕብረት" ከሚለውና ኤሚሊ ብሩነር "ንፁሕ የሆነ የአማኞች ሕብረት" ከሚለው ሐሳብ የካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን ለመለየት ሲሉ መግለጫውን አወጡ::[122]

የቫቲካን ሁለተኛ ካውንስል ሊደረግ ዋዜማ፣ ካርል ራህነር የሚባል የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ምሁር "መንፈስ ቅዱስና የቤተ ክርስቲያን መዋቅር" የሚል ሐሳብ አቀረበ::[123] ራህነር እንዲህ ዓይነት ሐሳብ ያመጣበት ምክኒያት በካሪዝማቲክ ሙቭ መንት እየሰፋና እያደገ መምጣት የፖፑን ሥልጣን የሚጋፋ ስለ መሰለው "የፖፑ ልዩና ምስያ የሌለው ሥልጣን ብቻ ነው የቤተ ክርስቲያንን አንድነት የሚጠብቅና እውነትንም ሊያስረግጥ የሚችለው::" ከሚለው ሐሳቡ በመነሣት "መንፈስ ቅዱስና የቤተ ክርስቲያን መዋቅር" የሚለውን ሐሳብ አሳደገ::[124] የራህነር ካሪዝማቲክ የቤተ ክርስቲያን መዋቅር ቤተ ክርስቲያኒቱ ለመንፈስ ቅዱስ ባላት ክፍትነት መንፈስ ቅዱስ መዋቅሩና የቤተ ክርስቲያን አፌሶች፣ የመንፈሱ መግለጫዎች መሆናቸውና፣

---

[121] See J. C. Gruden, *The Mystical Christ,* (St. Louis: n.p., 1936)124; E. Heston, *"The Dogmatic Preaching of the Fathers,"* ECC. Rev.. CHI; Stanislaus J. Grabowski, *"St. Augustine and The Doctrine of the Mystical Body of Christ," Catholic University of America,* www.google.com/St. Augustine and the Doctrine of the Mystical Body. (accessed November 25, 1013).
[122] Avery Dulles, *Models of the Church,* (Garden City, N.Y.: Doubleday, 1974).
[123] Karl Rahner, *"Do Not Stifle the Spirit," in Theological Investigations VII,* (New York: Hender, 1971), 72-87.
[124] Ibid., 76; Rahner, *"Observations of the Factor of the Charismatic in the Church," in Theological Investigations XII,* (New York: Seabury, 1974), 97.

በቤተ ክርስቲያን ያለውም አመራር ከመንፈስ ቅዱስ የመነጨ መሆኑ ለዚህ ሐሳብ ምሥክር እንደሆነ ያምናል::[125]

## 2. የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን:-

የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ስለ ቤተ ክርስቲያን ያላት ሥነ መለኮት የመነጨው ምሥራቅ ከነበሩት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ነው::[126] የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከምዕራብ ይልቅ "ለመንፈስ ቅዱስ ክፍት ነው" ማለት ይቻላል::[127] ይህ ግን ለክርስቶስ ወይንም ለሥላሴዎች ያላትን ቦታ ጥላለች ማለት አይደለም::[128] በምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነት "እግዚአብሔር አብ በቃልና በመንፈስ ቅዱስ ሁሉንም ያደርጋል::"[129]

የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን "ቤተ ክርስቲያን" የሚለውን ሐሳብ የሥላሴ ምሥጢር መግለጫ አድርጋ ትወስደዋለች:: "በምድር ላይ አንድነት በልዩነት ውስጥ የምትገልጥ ነች" ብላ ታምናለች::[130] "ቤተ ክርስቲያን" ("Ekklesia") "ለቅዱስ ቁርባን የሚሰበሰብ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጉባዔ ነው::" ጳጳሱ ይህንን የተቀደሰ ሥርዓት የሚያካሂድና የሚያስተዳድር ነው:: ምንም እንኳን እያንዳንዱ አጥቢያ በራሱ የቆመ ቢሆንም፣ ከዓለም አቀፍ ቤተ ክርስቲያን ግን የተቆራኘ ነው::[131] የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን "የክርስቶስ አካል" በክርስቶስ ሥራና በመን

---

[125] Rahner, *"Heresies in the Church Today?" in Theological Investigations XII*, (New York: Seabury, 1974), 117-141.
[126] C. N. Tsirpanlis, *Introduction to Eastern Patristic Thought and Orthodox Theology*, (Collegeville, MN: Liturgical Press, 1991).
[127] Robert Imbelli in his recommendations of Y. Congar's book, *I Believe in the Holy Spirit,* 3 vols. in one, (New York: Herder, 1997); Vladimir Lossky, *In the Image and Likeness of God,* ed. John H. Erickson and Thomas E. Bird, (New York: St. Vladimir's Seminary Press, 1985), chap. 4.
[128] See e.g., Nikos A. Nissiotis, *"Pseumatological Christology as a Presupposition of Ecclesiology, in Occumenica: An Annual Syposium of Ecumenical Research*, (Minneapolis, MN: Augusburg, 1967), 235-252.
[129] John Meyendorff, *Byzantine Theology: Historical Trends and Doctrinal Themes,* (New York: Fordham University Press, 1974), chap. 11.
[130] Vladimir Lossky, *Mystical Theology of the Eastern Church,* Crestwood, N.Y.: St. Vladimir's Seminary Press, 1976), 176-177; Kallistos Ware, *The Orthodox Church, rev. ed.,* (London: Penguin Press, 1993), 240; Kallistos Ware, *The Orthodox Way,* (New York: St. Vladimir's Seminary Press, 1999), 39.
[131] Kallistos Ware, *"Incarnation and Church," Paper presented at ICCOWE,* Prague, August 23-27, 2000.

ፊስ ቅዱስ ሙላት ላይ የተመሠረተ ነው ብላ ታምናለች::[132] ስለዚህም "የቤተ ክርስ ቲያን አንድነት:- የክርስቶስ አካል በመሆኗ እና የቤተ ክርስቲያን ልዩነት:- የመንፈ ስ ቅዱስ ሙላት በመሆኗ::"[133] "*እርስዋም አካሉና ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የእርሱ ሙላቱ ናት::*" (ኤፌ. 1:23) "ቤተ ክርስቲያን" በምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲ ያን አባባል:- "*የሥልጣን እርከንና መዋቅር ያላት* (Hierarchical) ብቻ ሳትሆን ካሪ ዝማቲክና ፔንተኮስታልም ጭምር ናት::"[134] ይህ የቤተ ክርስቲያኒቱ እምነት ምን ያህል በሥራና በተግባር ተገልጿል? የሚለው የሚገባ ብቻ ሳይሆን፤ መልስም የሚያ ስፈልገው አሳሳቢ ጉዳይ ነው!!!

**3. የሉተራን ቤተ ክርስቲያን "የቤተ ክርስቲያን ሥነ መለኮት" :-**

ሉተር እንደ ሪፎርሜሽን አባትነቱ ለመረዳት ካስፈለገ በሁለቱ በኩል የነበረውን ትግል መረዳት ያስፈልጋል:: በአንድ በኩል በድርጅታዊ እርከንና መዋቅር÷ እና በፖፑ የመጨረሻ ሥልጣን የምታምን የነበረችው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን፤ በሌላ በኩል ደግሞ "ኢንቱዚያስትስ" (Enthusiasts) የተባሉት "በመንፈስ ቅዱስ" የምንመራ ነን የሚሉና እውነተኛ ሪፎርመርስ እኛ ነን እያሉ የነበሩት ናቸው::[135] ሉተር በተለይም "ኪርሽ" ("Kirche") የሚለውን ቃል ስለማይወድ፤ "ቨርሳምላንግ" ("Versammlung -Assembly") እና "ገመይንደ" ("Gemeinde - Congregation) የሚሉትን ቃላት ይጠቀም ነበር:: ለሉተር "ቤተ ክርስቲያን የአማኞች ስብስብ (ጉባዔ) ነች::" እንዲያውም ሉተር "ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳን ሕብረት እንደሆነች አጥብቆ ይገልፅ ነበር:: ይህ አመለካከቱ ከሐዋርያት የእምነት መግለጫ ጋር የሚስማ ማ ነበር፤ እንዲህም ይላል:- "በሕብረት በመንፈስ ቅዱስ የተጠራ ሕዝብ::"[136] ሉተር ስለ "ቤተ ክርስቲያን" ምንነት የሰጠው በጣም የተሻለ ትርጉም እንዲህ የሚል ነው:-

---

[132] Vladimir Lossky, *"Concerning the Third Mark of the Church: Catholicity," in the Image and Likeness of God*, ed. John H. Erickson, (Crestwood, N.Y.: St. Vladimir's Seminary Press, 1985), 177-178, 157, 174.
[133] Ibid., 178-179; Meyendorff, *Byzantine Theology,* 174-175.
[134] Ware, *Orthodox Church,* 240-243, 249-250.
[135] Theodore G. Tappert, trans. ed. *The Book of Concord*, (Philadelphia,: Fortress, 1959); Eric W. Gritsch and Robert W. Jenson, *"Church body In Conflict," in Luthernaism :The Theological Movement and Its Confessional Writings*, (Philadelphia: Fortress, 1976), 124; Yves Congar, *I Believe in the Holy Spirit*, (New York: Crossroad Herder, 1997), 1: 139-140.
[136] Jaroslav Pelikan, ed. *Luther's Works,* (St. Louis: Concordia, 1955-1986); see further Paul Althaus, *The Theology of Martin Luther,* trans. Robert C. Schltz, (Philadelphia: Fortress, 1966), 294-323.

"የአማኞች ሁሉ ጉባዔ / ስብስብ ሆኖ፣ ወንጌል በንፅህናው የሚሰበክበትና የተቀደሱ ሥርዓቶች የሚካሄዱበት ነው::[137] ከዚህም እምነቱ የተነሣ ሉተር ስለ "ቤተ ክርስቲ ያን" ሲያስብ ድርጅታዊ መዋቅር ያላትና የበረከት ምንጭ እንደሆነች (በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እንደነበረው ዓይነት) ማሰብ አይፈልግም ነበር::[138] ሉተር በአንድ በኩል "ስውር ሕብረተ ሰብ" ነው፣ምክኒያቱም 'እምነት የማይታየውን የሚያስረግጥ' ስለሆነ፣ በሌላ በኩል "በግልፅ የሚታይ" ሕብረተ ሰብ ነው፣ ምክኒያቱም ወንጌል ስለሚሰበክና የተቀደሱ ሥርዓቶችም የሚካሄዱበት ስለሆነ ብሎ ያምን ነበር::

ሉተር የ"ቤተ ክርስቲያን" እውነተኛ ወይንም ሐሰተኛ የሚያስደርጋት መለኪያ ዋ "የመሪዎቹ ንፅህና ነው" ብሎ ያምን ነበር:: ሉተር ስለ "ቤተ ክርስቲያን" ንጽሕና ጥግ ወይም ፅንፈኛ የሆነ አስተሳሰብ አልነበረውም:: በአንድ በኩል የክርስቶስ አካል ስለሆነች ከጌታ የተነሣ እንደሆነች ቢያምንም፣ በውስጧ ያሉት መሪዎችም ሆነ ምዕ መን ግን "በጸጋ የዳነ ኃጢአተኛ ሕዝብ" እንደሆነም ያውቅ ነበር:: ነገር ግን "ቤተ ክርስቲያን" በመንፈስ ቅዱስ እስከተመራችና በቃሉና በቅዱስ ሥርዓቶች እስከ ተቀ ደሰች ድረስ ንጽሕት ነች ብሎ ያምናል::[139] ሉተር "ንጽሕት ቤተ ክርስቲያን" የሚ ለውን ሐሳብ አይቀበልም ነበር:: ሆኖም ግን "ቅዱሳት ሥነ ሥርዓቶች" ሕዝቡን ይቀድሳሉ፣ ምንም እንኳን ሥርዓቱን የሚያካሂዱት ካህናት የረከሱ ቢሆኑም::"[140] በዚህም ምክኒያት ሉተር ሰዎች የትኞቹ የተቀደሱ የትኞቹ ደግሞ ያልተቀደሱ እንደሆኑ ለመለየት የሚችሉበት ችሎታ የላቸውም ይል ነበር::[141]

ሉተር አንዱ እጅግ የሚታወቅበት ነገር "አማኞች ሁሉ የካህናት ጉባዔ" ናቸው የሚለው እምነቱ ነው::[142] "እናንተ...የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉስ ካህናት፣ ቅዱስ ሕዝብ፣ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ::" (1ጴጥ. 2:9) "የክርስቲያኖች የሕብረት ሥራ ከክርስቶስ ሊቀ ካህንነት የመነጨ ነው::" ብሎ ያምናል::[143] ለሉተር "የአማኞች ሁሉ ክህነት ቃሉን በመስበክ፣ የማስተዳደር ሥራና፣ ዲስፕሊን የማድረግ ሥልጣን

[137] Augusburg Confession 7: 1.
[138] Gritsch and Jenson, *Lutheranism,*130-131.
[139] Large Catechism, *In the book of Concord,* trans. and ed. Theodore G. Tappert, (Philadelphia: Fortress, 1959), 261-262.
[140] Augustburg Confessions 8: 1.
[141] Apology of the Augusburg Confession, 7: 1 - 8:17.
[142] See Althaus, *Theology of Martin Luther,* 313-318.
[143] See Pannenberg, *Systematic Theology*, 3: 373.

ሁሉ ያጠቃልላል::"[144] በአንፃሩም የቃሉ የስብከት አገልግሎት ግን ለዚሁ ከተጠሩት አገልጋዮች ጋር ሊጋጭና ልናምታታው የሚገባ አይደለም ብሎ ያምናል::[145] በሌላ በኩል ምዕመን ሁሉ የኃጢአትን ይቅርታ ለዓለም ሁሉ ለማወጅ ግን መብትና ሥልጣን እንዳለው ያምናል::[146]

ሉተር በሁለት መንገዶች ያምናል:: "ከታች" እና "ከላይ":: በአንድ በኩል ክርስቲያኖች ሁሉ ቃሉን፣ የቃሉ አገልግሎትና የቅዱሳን ሥነ ሥርዓቶች ሊያካሂዱ ይችላሉ:: በሌላ በኩል ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተምታታ ነገር እንዳይኖር ለዚህ አገልግሎት የተለዩና ("Ordained")፥ የተጠሩ አገልጋዮች ይህን ሥራ በቤተ ክርስቲያን ስም እንዲያካሂዱ ይገባቸዋል ብሎ ያምን ነበር::[147] በዚህ ምክኒያት የአገልግሎትን ቢሮ በያዘው ሰው መሃልና በምዕመን መሃል ያለው ልዩነት በአገልግሎት ላይ የተመሠረተ ነው::[148] በሌላ በኩል ደግሞ የክህነት ቢሮ የተመሠረተው በክርስቶስ ድርጅታዊ አሠራር ነው::[149] ይህ ግን የቅዱሳን ሁሉ "የንጉሥ ካህናት" መሆንን የሚያስጠፋ አይደለም::[150] ለአገልግሎቱ የተለዩና የተጠሩ ሰዎች መኖራቸውና የክህነት ቢሮ መኖሩ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥርዓት ባለው መንገድ ለማምለክና ለማገልገል ስለሚረዳ ነው (1ቆሮ. 14:40):: ስለዚህም ለአገልግሎቱ የተለዩና የተጠሩ ሰዎች እና "የካህናት ጉባዔ" በሆነው በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል እና ያለው ልዩነት የቃሉ አገልግሎትና የቅዱሳን ሥርዓቶች (Sacraments) ከማከናወን ጋር የተያያዘ ነው::[151]

የፕሮቴስታንት የክርስትና እምነት ክፍል የምዕመን ሁሉ "የካህናት ጉባዔ" መሆን ላይ ያተኮረ መመሪያ የሰጠው ከፍተኛ አስተዋፅዖ የሚከተሉት ናቸው:: አንደኛ አዲስ ኪዳን ስለ "ክህነት" ያለው መረዳት "የተለየና የተጠራ ግለሰብ" ላይ ሳይሆን የቅዱሳን ሁሉ "የንጉሥ ካህናት" መሆናቸውን ማስረገጡ ነው:: ሁለተኛው "በተለየ ወይም በተጠራ" ሰው መሃልና በተቀረው የእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል

---

[144] Augusburg 7: 25-26.
[145] Ibid., 6: 408; 11: 412.
[146] Ibid., 2: 722.
[147] Althaus, *Theology of Martin Luther,* 323-329; Miguel M. Garijo-Guembe, *Communion of the Saints: Nature and Structure of the Church,* trans. Patrick Madigan, (Collegeville, MN: Liturgical Press, 1994), 141; Augusburg 12: 189; 50: 633.
[148] Augusburg 6: 657.
[149] Ibid., 50: 647.
[150] Althaus, *Theology of Martin Luther,* 324-325.
[151] Ibid., 327.

ያለውን ልዩነት የጎላና የሰፋ እንዳይሆን ማድረጉ ነው። ሦስተኛው "ለክህነት አገልግሎት የተለየ ወይም የተጠራ" ሰው አገልግሎት ከምዕመን ሁሉ የክህነት አገልግሎት ጋር ምንም ግጭት ወይንም ተቃርኖ ሳይኖረው አብሮ እንዲፈስ አመለካከታችንን መቅረፁ ነው።

**4. የሪፎርምድ ቤተ ክርስቲያን ሥነ መለኮት:-**

የሪፎርምድ ቤተ ክርስቲያንን በምናስብበት ጊዜ መጠቀስ ያለባቸው ሁለት አባቶች አሉ። እነዚህም ጆን ካልቪንና አልሪች ዝዊንግሊ ናቸው። እነዚህ አባቶች ከሉተር ጋር አብረው የፕሮቴስታንትን ሪፎርሜሽን ለመምጣቱ እግዚአብሔር መሣሪያ አድርጎ የተጠቀመባቸው ናቸው። ካልቪን ከሉተር ጋር በመስማማት "እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቃል በግልጥነት የምትናገርና ቅዱስ ሥርዓቶችም የምታስተዳድር ነች" ብሎ ያምናል።[152] ነገር ግን ካልቪን ከሉተር በበለጠ ትክክለኛ እምነት በመያዝና የቅድስና ሕይወት ባለው የክርስትና ኑሮ አጥብቆ ያምን ነበር። ካልቪን "የዝዊንግሊን የእምነት መመዘኛ" እና "የአናባፕቲስት የሕይወት መመዘኛ" ከተቀበለ በኋላ "ቅዱሳን ሥርዓቶች አፈፃፀም" ጨምሮ ገልፆታል።[153] በካልቪን እምነት "የቤተ ክርስቲያን አባላት እምነታቸውን የሚገልፁ፣ ክርስትናቸውንም በሕይወት የሚያሳዩና ቅዱሳን ሥርዓቶችንም በመውሰድ በእግዚአብሔር አብና በልጁም በክርስቶስ ኢየሱስ ያላቸውን እምነት የሚያፀኑ ናቸው።"[154]

ካልቪን ከሉተር የተለየባቸው በርካታ ጉዳዮች ቢኖሩም፣ ጥቂቶቹን መግለፁ አስፈላጊ ነው። አንድም የአገልግሎት ሥርዓትና አሠራር በተመለከተ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አሠራር የእግዚአብሔር ቃል በግልፅ ያስቀመጠው መመሪያ አለ። ይኸውም "አገልጋይ" ("Minister") በሚለውና "ሽማግሌ" ("Elder") በሚለው መሃል ልዩነት አለ ብሎ ያምናል። ሁለተኛው ክርስቲያኖች በኃጢአት ሊወድቁ በሚደረገው ዲሲፕሊን ይለይ ነበር። ሉተር "ለሰውዬው ህሊና መተው አለበት" ብሎ ሲያምን፣ ካልቪን ግን ሕግ አጥባቂ (legalistic) ስለነበር "ቤተ ክርስቲያን ኃጢአት ያደረገ

---

[152] John Calvin, *Institutes of the Christian Religion*, ed. John T. McNeill, (Philadelphia: Westminster Press, 1960), 4. 1-12.

[153] C. Penrose, *St. Amant, "Reformation of the Church," in the People of God: Essays in the Believers' Church, ed.* Paul Basden and David S. Dockery, (Nashville, TN: Broadman, 1991), 213; See also Ronald Baiton, *The Reformation of the Sixteenth Century*, (Boston, Beacon, 1952), 115-116.

[154] Calvin, *Institutes,* 4. 1-8; See also Calvin, *Commentary,* (Grand Rapids, MI: Eerdmans, 1948), 1Corinthians 11: 2.

ውን ሰው መመሪያ ኖርአት ዲስፕሊን ማድረግ አለባት" ብሎ ያምን ነበር::[155] ካልቪ ን እንዲያውም ኢንስቲቱትስ በሚለው መጽሐፍ ውስጥ ዲሲፕሊንን በሚመለከት ጉዳይ አንድ ምዕራፍ ሙሉ ሰጥቶ ጽፏል::[156] ካልቪን በዚህ ጉዳይ ላይ የነበረው ጥብ ቅ አቋም በሕይወት ለውጥና በዶክትሪን ንፅህና በተመለከተ ወደ አንድ ወገን ያጋደ ለ ስለ ነበር፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን የነበረው አመለካከት "እምነት ቁልፍ ነገር ነው" ብሎ ያምን ከነበረው ዝዊንግሊ ሐሳብ ጋር ይጋጭ ነበር::[157] የካልቪን አቋም ከነበሩ ትና ብዙ ካነጋገሩ ጉዳዮች አንዱ ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት ጋር ያላት ግንኙነት የሚመለከት ነው:: በካልቪን እምነት ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት ጎን ለጎን የሚሄ ዱ፣ እርስ በርስ የሚደጋገፉና የሚተባበሩ ናቸው:: እነዚህ ሁለት ኃይላት አንድ ዓይነት ዓላማና ግብ አላቸው::

ስለዚህም ምድራዊ መሪዎችም ሳይቀሩ "የእግዚአብሔርን መንግሥት ማስፋት ና የዶክትሪንን ንፅህና መጠበቅ አለባቸው::" ብሎ ያምን ነበር::[158] ለካልቪን "ቤተ ክርስቲያን" በቅድሚያ "የሚታይ" ("Visible") ሕብረተ ሰብ ነው:: ካልቪን "ቤተ ክርስቲያንን "የታመኑት እናት"÷ እንደገና በመውለድና በደህንነት ውስጥ ለተገኘ ሕዝብ "እናት" አድርጎ ይገልፃታል::[159] ካልቪን ከዚህ የጠበቀ አቋሙ የተነሣ ማንም አማኝ "ከምትታየዋ ቤተ ክርስቲያን" ፈፅሞ መለየት የለበትም፣ እንዲያውም በመን ቀጥቀጥ የጌታን እራት ሊወስድ ይገባዋል::" ብሎ ያምናል::[160] ካልቪን በአንፃሩ ደግሞ "በማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን" ("Invisible Church") ከማመኑም በላይ "የተ መረጡት ስብስብና እውነተኛ" ብሎ ይገልፃታል:: ካልቪን "የምትታየዋ ቤተ ክርስ ቲያን" እና "የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን" ሁለት የተለያዩ ቤተ ክርስቲያኖች ሳይሆ ኑ ነገር ግን አንድ ቤተ ክርስቲያን ሆኖ ሁለት ገፅታ ያላት እንደሆነች ሙሉ በሙሉ ያምናል::[161] ካልቪን የሚያምነው ክርስቶስ ያቀረበውን የደህንነት ዕድል በእውነት

---

[155] Baiton, *Reformationof the Sixteenth Century,* 116. Strangely enough, Francois Wendel, in his excellent study on Calvin, disagrees, *Calvin: Origins and Development of Religious Thoughts*, (New York: Harper & Row, 1963), 301.
[156] Calvin, *Institutes,* 4: 22.
[157] See further P. D. L. Avis, *"The True Church in Reformation Theology," Scottish Journal of Theology* 30 (1977): 326-332.
[158] Calvin, *Commentary,* Isaiah 49: 23.
[159] See further John W. Riggs, *"Emerging Ecclesiology in Calvin's Baptismal Thought, 1536-1543," Church History* 64, no. 1 (1995): 37-38.
[160] Calvin, *Institutes,* 4: 1-7.
[161] Riggs, *"Emerging Ecclesiology,"* 41.

የተቀበሉት ጥቂቶች (ያውም የተመረጡት ማለትም በእግዚአብሔር የታወቁት) ብቻ እንደሆኑ ነው::[162] ለካልቪን "የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን" እግዚአብሔር በመ ጨረሻው ዘመን ለፍርድ በሚመጣበት ጊዜ በሙላት የምትገለፀው ስትሆን፤ "የምት ታየዋ ቤተ ክርስቲያን" ደግሞ ከነ ድካሟና ውድቀቷ በክርስቲያኖች ሁሉ ልትከበር ይገባታል::

በሃያኛው ምዕተ ዓመት ተነስቶ የነበረው "የቤተ ክርስቲያን አባት" ካርል ባርዝ ነው:: ካርል ባርዝ የሪፎርሜሽን አባቶች የነበሩት ካልቪንና ዝዊንግሊ የነበራቸውን የቤተ ክርስቲያን ሥነ መለኮት ላይ መሠረት በማድረግ የሪፎርምድ ቤተ ክርስቲያ ን ገጽታን በብዙ መልኩ የለወጠ ምሁር ነው:: ባርዝ በሦስት የሥነ መለኮት መሠረ ቶች በመነሳት የቤተ ክርስቲያን ምንነት ለመግለፅ ተጠቅሞባቸዋል:: እነዚህም የመ ንፈስ ቅዱስን (Pneumatology)፥ የክርስቶስን (Christology)፥ እና የእግዚአብሔር ቃል ጉዳዮች ናቸው::[163] ለባርዝ "የቤተ ክርስቲያን" ምንነት ለመተርጎም የሚጠቀ መው "የክርስቶስ አካል" የሚለው መግለጫ ነው::[164] ባርዝ "ቤተ ክርስቲያንን" የሚ ያያት"ሕይወት ያላት" (Dynamic) እንጂ፥ በአንድ ቦታ ላይ የረጋች፥ የማትንቀሳቀ ስና ሕይወት የሌላት" እንደሆነች አያምንም:: ስለዚህም "ሕብረተ ሰብ" ("Community")እና "ማሕበረ ምዕመናን" ("Congregation") የሚለውን ቃል መጠቀ ም ይመርጥ ነበር::[165]

ባርዝ በአንድ በኩል የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አቋም የነበረውን የተለጠጠ የቅ ዱስ ሥርዓቶች እምነትን፤ በሌላ በኩል ደግሞ የአናባፕቲስቶች አቋም የነበረው "ሞራላዊነትን" ይቃወም ነበር:: በባርዝ እምነት የመጀመሪያው ሰብዓዊ ሥርአት ሆኖ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ የሚያቃልል ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ሰው ምንም ዓይ ነት ስህተት የሌለው (Infallible) እንደሆነ የሚያስመስልና በሌላ ላይ እንድንፈርድ ያደርጋል::[166] ባርዝ ሌላ ሦስተኛ አማራጭ ያመጣው "የመመረጥ ዶክትሪን" ሆኖ፥

---

[162] Calvin, *Institutes,* 3: 22-27; Riggs, *"Emerging Ecclesiology"*, 42.
[163] For Karl Barth's Pneumatological Ecclesiology, see further James J. Buckley, *"A Field of Living Fire: Karl Barth on the Spirit and the Church," Modern Theology* 10, no. 1 (1994): 81-102.
[164] Barth, *Church Dogmatics,* 211, 149; See further Nicholas M. Healy, *"The Logic of Karl Barth's Ecclesiology: Analaysis, Assessment and Proposed Modifications," Modern Theology* 10, no. 3 (1994): 254-257.
[165] Barth, *Church Dogmatics,* 6/1, 650.
[166] Ibid., 694, 696.

በእርሱ አባባል ይኼ እውነተኛ ክርስቲያኖችን ለመለየትና በእውነተኛ ቤተ ክርስቲ ያን ውስጥ ያሉትን አባላት እነማን እንደሆኑ ለማወቅ ይረዳል ብሎ ያምናል::[167]

ለባርዝ በቤተ ክርስቲያንና በመንግሥት መካከል ምንም ዓይነት ውህደት መኖር እንደ ተረገመ ሐሳብ (Anathema) ነበር፣ ምክኒያቱም መንግሥት የዓለም ክፍል ነው::[168] መንግሥት የሚያስፈልገው "ነፃ የሆነች ቤተ ክርስቲያን" ያለውን የጥሪው ውሱንነት የምታሳስብ፥ ወደ አመፅ ወይንም ወደ ግድያ እንዳይሄድ የምትከለክል ነች::[169]

### 5. የ"ነፃ ቤተ ክርስቲያን" ሥነ መለኮቶች:-

### "ቤተ ክርስቲያን፡- የአማኞች ሕብረት"

ስለ "ቤተ ክርስቲያን" ያለው መረዳት ከነበረው ባህላዊ፥ ማለትም የሥልጣን እርከንና መዋቅር ከሚያምን፥ ማሳተፍ ወደሚታይበት አመለካከት በብዙ እየተለወጠ እንዳለ የሚታይ እውነት ነው:: በተለይም የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች "ነፃ የሆነ ክርስትና" ወደሚለማመዱበት መድረክ እየሄዱ ነው::[170] እንዲያውም በቅርቡ ከፖፕነት በፈቃዳቸው ራሳቸው የወረዱት ጆሴፍ ካርዲናል ራዚንገር እንዲህ የሚል ሐሳብ በሪፖርታቸው ላይ አቅርበዋል:-

"በእኔ አመለካከት ነባራዊ የሆነ የካቶሊክ የ'ቤተ ክርስቲያን' ትርጉም በግልጽ ሳይጣል፥ ቀስ በቀስ ግን ደብዛው እየጠፋ ነው:: የ'ቤተ ክርስቲያን' ፅንሰ ሐሳብ በካቶሊክ አስተሳሰብና በካቶሊክ ሥነ መለኮት፥ እንደ አዲስ እየበቀለ የሄደው የፕሮቴስታንት ነው ባይባልም፥ የሰሜን አሜሪካ 'ነፃ ቤተ ክርስቲያኖች' ሙሉ በሙሉ የሚያንጸባርቅ ነው::"[171]

---

[167] Ibid., 696.
[168] Ibid., 4/2, 688.
[169] Ibid., 687.
[170] Miroslav Volf, *After Our Likeness: The Church as an Image of the Trinity*, (Grand Rapids, MI: Eeredmans Publishing House, 1998), 12.
[171] Joseph Cardinal Ratzinger, *The Ratzinger Report: An Exclusive Interview on the State of the Church*, with Vittoriv Messori C. Sao, (Francisco, CA: Ignatius, 1985), 46.

እንዲህ ዓይነቱ አሠራር “ማሕበረ ምዕመናን የማደራጀት ሂደት” ይባላል::[172] ሐርቪ ኮክስ የሚባለው ጸሐፊ የሊበሬሽን ቲዮሎጂ ዋና አቀንቃኝ የሆነውን ሊዮናርዶ ቦፍን ለመቃወም ሲል “የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እረፍት የሌለው መንፈሳዊነት በሕብረ ተ ሰቡ ውስጥ እየጠበበ መሄዱንና አፍራሽነቱን እንዴት ሊቋቋሙት ይችላሉ?” ይላ ል::[173] ሚሮስላቭ ቮልፍ እነዚህ አስተሳሰቦች ማንም ሰው ሊቃወም ቢሞክርም፣ በቤ ተ ክርስቲያን የታሪክ ዕድገት እየሰፉኑና እያደጉ መምጣታቸው የማይካድ ሐቅ እን ደሆነ ያምናል:: ይህን ሐሳቡን ሲያፀና “የነፃ ቤተ ክርስቲያን ሞዴል” በዓለም ላይ እየተካሄደ ባለው የዓለም ሕብረተ ሰብ ለውጥ ምክኒያት የተወለደ አስተሳሰብ መሆኑ የማያጠራጥር ነው” ይላል::[174]

የ“ነፃ ቤተ ክርስቲያን” ሥነ መለኮት አጀማመር ከአክራሪ የሪፎርሜሽን ክፍል (ለምሳሌ:- የባፕቲስት ሙቭመንት) ("The Radical Reformation") እና ከአናባፕቲ ስት፣ በኋላም ከባፕቲስት ሙቭመንት የመነጨ ነው::[175] “ነፃ ቤተ ክርስቲያኖች” እግዚአብሔር ራሱን በገለጠበት በእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን ላይ የተመሠረቱ አድርገው ራሳቸውን ከማየታቸው በተጨማሪ፣ ያለ ምንም መካከለኛ “የሰው አማላ ጅ” ከእግዚአብሔር ጋር የግንኙነት መሥመርና “ሰው ሠራሽ ከሆነ ሥርዓት ይልቅ፣ በቀጥታ ከጌታ ጋር ሕብረት እንዳላቸው ያምናሉ::[176] ስለዚህም “ቅዱስ ሥርዓቶችን ” ማካሄድም ይሁን÷ ወይንም በጣም ጥብቅ የሆነ የአምልኮ ሥነ ሥርዓት ማካሄድም አያምኑም:: የመንፈስ ቅዱስ አመራርና አሠራር እውነተኛ አምልኮ ለማካሄድ ወሳ ኝ እንደሆነ ያምናሉ:: በ“ነፃ ቤተ ክርስቲያኖች” የሥልጣን እርከንና መዋቅር ያለው

---

172 Russell Chandler, *Racing Toward 2001: The Forces Shaping America's Religious Future*, (Grand Rapids, MI: Zondervan Publishing House, 1992), 210; Volf, *After Our Likeness*, 13.

173 Harvey Cox, *The Sliencing of Leonardo Boff: The Vatican and the Future of World Christianity*, (Oak Park, Ill.: Meyer-Stone, 1988), 17.

174 Volf, *After Our Likeness,* 13.

175 See further James W. McClendon, Jr. *Doctrine: Systematic Theology*, vol.2 (Nashville, TN: Abingdon, 1994); See also John J. Kiwiet, *"Anabaptist Views of the Church," in the People of God: Essays on the Believers' Church,* ed. Paul Baden and David S. Dockery, (Nashville, TN: Broadman, 1991), 225-234; Michael Novak, *"The Free Churches and the Roman Catholic Church: The Conception of The Church in Anabaptism and in Roman Catholicism: Past and Presnt," Journal of Ecumenical Studies* 2 (1965): 429.

176 See further Congar, *I Believe In The holy Spirit*, 1: 141-143.

አሠራር ተቀባይነት የለውም:: እያንዳንዱ አማኝ በግሉ ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግንኙነት ሊኖረው ይችላል ብለው ያምናሉ::

አንደኛ "ቤተ ክርስቲያን" በ"ነፃ ቤተ ክርስቲያኖች" እምነት የክርስቶስ ነች እንጂ ማንም በዋናነት/ በአውራነት የሚይዛት አይደለችም:: ሌላው ደግሞ የ"ቤተ ክርስቲያን" አባል ለመሆን በግለሰቡ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ነው:: ስለዚህም "የጥ ምቀት ሥነ ሥርዓት መካሄድ ያለበት "አንድ ሰው በክርስቶስ አምኖ ከዳነ በኋላ እን ጂ÷ ለህፃናት መደረግ የለበትም::"ብለው ያምናሉ:: ሦስተኛ "ነፃ ቤተ ክርስቲያኖች "ከዓለም መለየትና የቅድስና ሕይወት መኖርን "በጥብቅ ያምናሉ÷ ያስተምራሉም:: አራተኛው "ቤተ ክርስቲያን" በርዋን ከፍታ ሕዝብ እንዲመጣ የምትጠብቅ ሳትሆን ፤ ሕዝቡን በወንጌል ለመድረስ "የሚሸን ተልዕኮና ጥሪ ያላት" እንደሆነች ማመናቸ ው ብቻ ሳይሆን፤ በሥራም ይገልፁታል:: አምስተኛው በ"ቤተ ክርስቲያን" ውስጥ የቤተክርስቲያን ዲሲፕልንና የውስጥ ዲሲፕልን መኖር እንዳለበት አጥብቀው ያምኑ በታል:: ስድስተኛ: "ለክህነት አገልግሎት ከተለዩ / ከተጠሩ" ("Ordained Ministers) አገልጋዮች ይልቅ፤ "በአማኞች ሁሉ የክህነት አገልግሎት" ያምናሉ:: ሰባተኛው:- "ቤተ ክርስቲያን" ከሴኩላሩ መንግሥት ጋር በጣምራ ማስተዳደር እንዳለባት አያም ኑም:: ይልቁንም የቤተ ክርስቲያን ክብርና ንፅህና መጠበቅ እንዳለበት ያምናሉ::[177]

አንዱ ዋና የ"ነፃ ቤተ ክርስቲያኖች" እምነት "የአማኞች ሁሉ የክህነት አገልግ ሎት" በ 1ጴጥሮስ 2:9 ላይ የተመሠረተውና በክርስቶስ የሊቀ ካህንነት ፍፁም ሥራ ና አገልግሎት የተንግ የክህነት አገልግሎት ከሌዊ ነገድ ወጥቶ ወደ ይሁዳ ነገድ÷ በእርሱም ምክኒያት ለሁላችን የተሰጠ አገልግሎት በመሆኑ ላይ የተመሠረተ (ዕብራ ውያን 7:1-14) ነው::[178] አብዛኛዎቹ "ነፃ ቤተ ክርስቲያኖች" "ለክህነት አገልግሎት

---

[177] Frankllin H. Little, *The Concept of the Believers' Church," in the Concept of the Believers' Church*, ed. James Leo Garrett, (Scottsdale, Penn.: Herald, 1969), 15-33; William R. Easter, Jr. *"A Beleiving People: Historical Background," in the Concept of the Believers' Church,"* ed. James Leo Garrett, (Scottsdale, Penn.: Herald, 1969), 102; Williams, *"The Believers' Church,* ed. Paul Basden and David S. Dockery, (Nashville, TN: Broadman, 1991), 325-332.

[178] See James Leo Garrett, *Systematic Theology: Biblical, Historical and Evangelical*, (Grand Rapids, MI: Eerdmans, 1995), 2: 560-563; Robert G. Walton, *The Gathered Community,* (London: Carey, 1946), 102; Herschel H. Hobbis, *You Are Chosen: The Priesthood of Believers,* (San Francisco, CA: Harper & Row, 1990); Paul Beasley-Murray, *"The Ministry of All and The Leadership of Some: A Baptist Perspective," in Anyone For Ordination?* ed. Paul Beasley-Murray, (Tunbridge Wells, UK: Monarch,

የተለዩ ወይ የተጠሩ" ቢኖሯቸውም፣ ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በጣም የተለየና፣ "ለአገልግሎት መለየት ወይም መጠራት" ሰውዬው ለአገልግሎት መጠራቱ የአደባባ ይ መግለጫ ወይም ማስረገጫ እና እግዚአብሔር የጠራውን ጥሪ ማረጋገጫ እንጂ፣ እንደ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የሥልጣን እርከን መወጣጫ አይደለም::[179]

## 6. የፔንትኮስታልና የካሪዝማቲክ አብያተ ክርስቲያናት

### "የቤተ ክርስቲያን ሥነ መለኮት:- ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ውስጥ"

ያለፈው ሃያኛው ምዕተ ዓመት በፔንትኮስታል ሙቭመንትና[180] በካሪዝማቲክ ሙቭመንት[181] መነሣት ምክኒያት አስደናቂ የሆነ የቤተ ክርስቲያን ዕድገት የታየበ ት ዘመን ነው:: በመጀመሪያ የፔንትኮስታል ሙቭመንት የጀመረው ጥር 1, 1901 (እ.አ.ዘ.አ.) ሆኖ ቻርለስ ኤፍ ፓርሃማ በሚባል ሰው ቶፔካ፣ ካንሳስ ውስጥ በሚገኘ ው ቤቴል የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ውስጥ የነበሩት ተማሪዎች የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በማጥናት ላይ እንዳሉ መንፈስ ቅዱስ በላያቸው ላይ ወረደባቸው፣ በልዩ ልሳኖችም መናገር ጀመሩ:: ከጥቂት ዓመታት በኋላ "የቅድስና ሰባኪ" (በነበረው ጥቁር አሜሪካዊ ዊልያም ጄ ስሞር እና አብረውት በነበሩት ጥቂት ወንድሞች ላይ ሎስ አንጀለስ ( ካሊፎርንያ) በሚገኘው አዙሳ ስትሪት (AZUSA STREET) ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው፣ በልዩ ልዩ ልሣኖችም መናገር ጀመሩ:: ከ1906 ዓ. ም. (እ.አ.ዘ.አ.) ጀምሮ በአሜሪካና በዓለም ሁሉ ከዳር እስከዳር የመንፈስ ቅዱስ አስደናቂ የሆነ ሥራ ተጀመረ:: በአጭር ጊዜ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ በካናዳ፣ በእንግሊዝ፣ በስካንዲነቭያን አራቱም አገሮች (ስዊድን፣ ኖርወይ፣ ዴንማርክ ና ፊንላንድ)፣ በጀርመን፣ በእስያ፣ በአፍሪካና በላቲን አሜሪካ እንደ ሰደድ እሳት ተሠራጨ!!!

---

1993), 157-174; Cyril Eastwood, *The Priesthood of All Believers: An Examination of the Doctrine From The Reformation to the Present Day,* (London: Epworth, 1960), 164-171.

[179] See further Fisher Humphreys, *"Ordination in the Church," in the People of God,* 288-298; Volf, *After Our lIkeness,* 245-247; Balthasar Fischer, *"Catholic Liturgy in the Light of Vatican II and The Post-Conciliar Reform of Liturgy," One in Christ* 13 (1977): 28-30.

[180] S. M. Burgess and G. McGee, ed. *"The Pentecostal and Charismatic Movements," in Dictionary of Pentecostal and Charismatic Movements*, (Grand Rapids, MI: Zondevan, 1988), 1-6; Walter J. Hollenwege, *Pentecostals*, (Londoh: SCM Press, 1972); Hollenwege, *Pentecostalism: Origins and Developments Worldwide*, (Peabody, Mass.: Hendrickson, 1998).

[181] Peter Hocken, *"The Charismatic Movement," in the Dictionary of Pentecostal and Charismatic Movements,*, 130-160; *Pneuma* vol. 6, no. 2 (1994) and vol. 18, no. 1 (1996).

ከአምሳ ዓመት በኋላ ይህ የመንፈስ ቅዱስ እድሳት በቆዩት አብያተ ክርስቲያና ትም መግባት ስለ ጀመረ "የካሪዝማቲክ እድሳት ሙቭመንት" በአሜሪካ ውስጥ በ1960 ዓ.ም. (እ.አ.ዘ.አ.) ተጀመረ::[182] የካሪዝማቲክ ሙቭመንት እያደገ ሲመጣ ወደ ሌሎች የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት፥ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንና በመጨረሻም የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መስፋፋት ጀመረ:: ይህ የካሪዝማቲክ ሙቭመንት በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የመንፈሳዊ ሕይወት ልዩና የጠለቀ ጣዕም እንዳለው እንዲያውቁና እንዲለማመዱትም ረድቷል!!!

ከዚህም የተነሣ የፔንትኮስታል/ ካሪዝማቲክ ሙቭመንት በሃያኛው ምዕተ ዓመት ትልቁና ዋነኛ የፕሮቴስታንት ክፍል እንደሆነ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የታየ ነው::[183] ዋልተር ጄ ሆለንወገር የሚለው ጸሐፊ:- "ከዜሮ ተነሥቶ በዘጠና ዓመታት ውስጥ ተሰምቶና ታይቶ የማይታወቅ ነው" ይለዋል::[184] በአሁኑ ዘመን የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ትልቋ ቤተ ክርስቲያን ከሆነች፤ ሁለተኛው ትልቁ ደግሞ የፔንትኮስታል ሙቭመንት እያደገና እየጎለመተ መመጣቱ ምሥክር ነው:: የፔንትኮስታል ሙቭመንት ገፅታ የሚያሳዩ ምክኒያቶች ብዙ ባህሎችን፥ ብዙ ብሔሮችን፥ እና በልዩ ልዩ ነገዶች መካከል መስፋፋቱ ናቸው::[185]

የፔንትኮስታል ሙቭመንት ከአንድ የተንጣለለ የሥነ መለኮት አስተሳሰብ እንደ ተነሣ ከማሰብ ይልቅ፤ ከታችኛው ደረጃ (ከሥር) የተነሣ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ እንደሆነ ልናውቀው ይገባል:: ጆን ሩትቨን የሚባል ጸሐፊ:- "የፔንትኮስታል እንቅስ

---

[182] Henry I. Lederle, *Treasures Old and New: Interpretations of "Spirit Baptism," in the Charismatic Renewal Movement*, (Peabody, Mass.: Henrickson, 1988), XIII.

[183] L. Grant McClung, Jr. "David Barrett's Description of the Pentecostal/ Charismatic Tradition, now numbering more than 400 million and growing by 19 million a year and 54, 000 a day, is that it comes in an 'amazing variety' of 38 major categories, 11, 000 Pentecostal denomiations, and 3, 000 independent Charismatic denominations spread across 8, 000 ethno-linguistic cultures and 7, 000 languages. A cross section of worlswide Pentecostal/ Charismatic who is more urban than rural, more female than male, more Third World (66%) than Western World, more impoverished (87%) than affluent, more family oriented than individualistic, and on average younger than eighteen" (*"Pentecostal/ Charismatic Perspectives on a Missiology for the Twenty-First Century," Pneuma* 16, no. 1 (1994): 11.

[184] Walter J. Hollenweger, *"From Azusa Street to the Toronto Phenomenon: Historical Roots of the Petecostal Movement," Concilium* 3 (1996): 3.

[185] See A. A. Anderson and W. J. Hollenweger, eds. *Petecostals After a Century: Global Perspectives on a Movemnt in Tradition*, (Sheffield, UK: Sheffield Academic Press, 1999); Vinson Synao, *"Pentecostalism: Varieties and Contributions," Pneuma* 8, no. 2 (1986): 34-36.

ቃሴ እምነት በመንፈሳዊ ስጦታዎች ላይ ሆኖ፣ ተአምራታዊ ፈውስ፥ ትንቢታዊ መልዕክትና በልሳኖች መናገር ከመንፈስ ቅዱስ የመነጩና የተሰጡ ከመሆናቸው የተነሣ የትኛውም ቤተ ክርስቲያን ልትቀበለው የሚገባ እውነት ነው" ይላል::[186]

የፔንትኮስታል ሙሽመንት ዋና ትኩረት ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀና ግላዊ የሆነ ሕብረት በማድረግ ላይ የተመሠረተ መንፈሳዊነት ነው::[187] ይህንን መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ለመረዳት የግል መንፈሳዊ ልምምድ ላይ የተመረኩዘ እንደሆነ ልናስተውል ይገባል:: የእግዚአብሔርን አብሮነት መለማመድና በእርሱ ህልውና ውስጥ መግባት ነው::[188] የፔንትኮስታል ሙሽመንት አንዱ መለያው "አምልኮ" በእግዚአብሔር ህላዎት ውስጥ መግባትና በመንፈስ ውስጥ ሆኖ በፊቱ እንደ ውሃ መፍሰስ፥ ማምለክና መስጠት ነው:: በተጨማሪም መንፈሳዊ የፀጋ ስጦታዎችን መለማመድን፣ በልሳን መናገርን፣ የትንቢት ስጦታ መጠቀምን፥ ለፈውስና ለተአምራት መፀለይን፣ ከሁሉ በላይ ደግሞ በግል ከጌታ ጋር መገናኘትን ያጠቃልላል:: ሌላው ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ለግል አምልኮ፣ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ማግኘት ለአገልግሎትና ለወንጌል ሥራ ምስክርነት እንደሆነ ያምናል:: ከዚህ የተነሣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በግልም ሆነ የጀማ ስብከተ ወንጌል፥ ወንጌልን ለመስበክ እጅግ ወሳኝ እንደ ሆነ የፔንትኮስታል ሙሽመንት ሙሉ በሙሉ ያምናል:: በተጨማሪም የእግዚአብሔር መለኮታዊ አሠራር እንዲገለጥም ይመኛል፣ ይፀልያል፣ ሁኔታዎችንም ያመቻቻል::[189]

የፔንትኮስታል ሥነ መለኮት "የቤተ ክርስቲያንን" ምንነት የሚገልፅ ባሕርዩን ለመረዳት የሚረዳው "ሙሉ ወንጌል" የሚለው እምነት የሚገልፁ አምስት መግለጫዎች ስናስተውል ነው:: እነዚህ አምስት መግለጫዎች:- የፔንትኮስታል ሙሽመንት ሥነ መለኮት የሚያንፀባርቁ ናቸው::

- ❖ በእምነት መጽደቅ በክርስቶስ እንደሚገኝ፣
- ❖ በእምነት በክርስቶስ ጸጋና ሥራ መቀደስ፣
- ❖ ለሰው ሁሉ የተዘጋጀ፥ በክርስቶስ ሞት የተገኘ የሥጋ ፈውስ፣
- ❖ የክርስቶስ ዳግም መምጣት (አስቀድሞ ቤተ ክርስቲያንን ለመውሰድ)፣

[186] Jon Ruthven, *On The Cessation of the Charismata*, (Sheffield, UK: Sheffield Academic Press, 1993), 14.
[187] See Daniel E. Albrecht, *Rites in the Spirit: A Ritual Approach to Pentecostal/ Charismatic Spirituality*, (Sheffield, UK: Sheffield Academic Press, 1999).
[188] Albrecht, *"Pentecostal Spirituality: Looking Through the Lens of Ritual,"* *Pneuma* 14, no. 2 (1996): 21.
[189] Ibid., 23.

◆ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት፥ በልሳን መናገር የተረጋገጠ::[190]

የፔንትኮስታል ሙቭመንት ስለ "ቤተ ክርስቲያን" ያለው ሥነ መለኮት መነጋገር መቻል አለመቻሉን የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ምሁር የሆነው ፓውል ዲ ሊ በጥያቄ መልክ ያቀርበዋል:: "የፔንትኮስታል እንቅስቃሴ ሙቭመንት ስለሆነ ስለ ቤተ ክርስቲያን ያለውን ሥነ መለኮት መነጋገር የሚገባ ጉዳይ ነውን? <u>ፔንትኮስታሎች ከጅማሬአቸው የምሥራቹን ወንጌል ለዓለም ሁሉ ለማሰራጨት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተሞልተው በብዙ ትጋት ሲያሰራጩ በመቆየታቸው ምክኒያት፣ የራሳቸውን ቤተ እምነት ለማቋቋም ምንም አልገደዳቸውም::</u> የጌታ ዳግም መምጣት የወንጌልን አጣዳፊነትና የእግዚአብሔር መንግሥት ጉዳይ ስለያዛቸው ስለ 'ቤተ ክርስቲያን' አሠራር (Ecclesiology) ማሰብ አስፈላጊ መስሎ አልታያቸውም፣ ወይንም በሁለተኛ ደረጃ መታሰብ እንዳለበት አመኑ::"[191] ምናልባት መጠቀስ ያለበት መጠነኛ የሆነ ግን አስፈላጊ አስተዋፅዖ በኤም ኤል ሆጅስ የተሰጠው የፔንትኮስታል ሙቭመንት ሥነ መለኮት ነው::[192] ከዚህ ጋር በተያያዘ ፒተር ሆከን በመጣጥፉ ላይ "የቤተ እምነት ማቋቋም በኤፌሶን 4: 11 ላይ መሠረት በማድረግ የአምስት ቢሮዎች ሥራ ለማጠናከር ለሚፈልጉት ብቻ ጠቀመ እንጂ፣ የፔንትኮስታል ሙቭመንት የ 'ቤተክርስቲያን' አሠራር አመለካከት ለማንፀባረቅ አልረዳም::"[193] ለዚህ ነው የፔንትኮስታል ሙቭመንት ስለ "ቤተ ክርስቲያን" አሠራር በተመለከተ "ጊዜያዊና በየጊዜው መሻሻ

---

190 Steven J. Land, *Pentecostal Spirituality: A Passion for the Kingdom*, (Sheffield, UK: Sheffield Academic Press, 1992), 18; Hollenweger, *"After Twenty Years' Research on Pentecostalism," International Review of Missions* 75 (January 1986): 6:; Hollenweger, *"From Azusa Street,"* 3-14; See also Veli-Matti Karkkanen, *Pneumatology: The Holy Spirit i Ecumenical, International and Contextual Perspective*, ( Grand Rapids, MI: Baker Books, 2002, 87-98.

191 Paul D. Lee, *Pneumatological Ecclesiology in the Roman Catholic -Pentecostal Dialogue: A Catholic Reading of the Third Quinquennium*, (1985-1989) (Dissertation ), 15.

192 Peter Kuzmic and Miroslav Volf, *("Communio Sanctorum: Toward Theology of the Church as a Fellowship of Persons,"* A Postion Paper read at the International Roman Catholic-Pentecostal Dialogue, Riano, Italy, May 21-26, 1985 (Unpublished), 2; George Vandervelde, *"Ecclesiology in the Breach: Evangelical Soundings," Evangelical Review of Theology*, 23, no. 1 (1999): 29-51.

193 Peter Hocken, *"Theology of Church," in The Dictionary of Pentecostal and Charismatic Movements*, ed. S. M. Burgess and G. B. McGee, (Grand Rapids, MI: Zondervan, 1988), 213.

ል የሚችል" ሆኖ ያስቀመጠው::[194] የፔንትኮስታል ሙቭመንት የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊነት፥ ይልቁንም 'የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን' ላይ ልዩ ትኩረት ስለሚሰጥ፥ በሐዋርያት ዘመን የነበረውን መንፈስ ለማደስ የሚያስችል የቤተ ክርስቲያን አሠራር (polity) ላይ የሚያንፀባርቅ ነው::[195]

በ1972 ዓ.ም (እ.አ.ዘ.አ.) ፔንትኮስታሎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጋር መነጋገር መጀመራቸው በጣም ጥሩ ሁኔታዎችን ፈጥሯል:: ይህ ውይይት በሰፊው ከመካሄዱም በላይ፥ ፔንትኮስታሎችን ስለ "ቤተ ክርስቲያን" እና ስለ ሕይወቷና አገልግሎትዋ የበለጠ አጥልቀው እንዲያስቡ አድርጎአቸዋል:: የሦስተኛው የውይይት ጉባዔ (1985-1989) "ቤተ ክርስቲያን" 'ኮይኖንያ'- 'የወንድማማች ሕብረት' ከሚለው ሐሳብ አንፃር ነበር የተደረገው::[196] አንዱ "የቤተ ክርስቲያን" አሠራር በትክክል ለማስቀመጥ ያስቸገረው የመንፈስ ቅዱስ (ካሪዝማ) ከቤተ ክርስቲያን ድርጅታዊ አሠራር ጋር ያለው ግንኙነት ነው::[197] የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በዚህውይይት ያተኮረችው በቤተ ክርስቲያን የሥልጣን እርከንና መዋቅር፣ ለአገልግሎትበተለዩ ሰዎች፣ የቤተ ክርስቲያን ሥልጣን፣ እና በቅዱስ ሥርዓቶች ላይ ሲሆን፣ የፔንትኮስታል ሙቭመንት ደግሞ የጸጋ ስጦታዎች በነፃነት በቤተ ክርስቲያን እንዲት መፍሰስና መሥራት እንዳለባቸው የሚለው ሐሳብ ዋና ትኩረታቸው ነበር::ሆኖም የፔንትኮስታል ሙቭመንት በቀላሉ ያዩት ከነበረው በካሪዝማና በቤተ ክርስቲያን ድርጅታዊ አሠራር መካከል የደመቀ ልዩነት እንዳላቸው ከማጉላት ይልቅ፣ ከዚያ አልፈው ለመሄድና "ቤተ ክርስቲያን ካሪዝማቲክ የሆነችና መዋቅር ያላት ወደሚለው መረዳት ለመምጣት ሙሉ በሙሉ ያመኑበትና የተቀበሉበት ጊዜ ነው::

በፔንትኮስታል ሙቭመንትና ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መካከል የነበረው ውይይት የሚያመለክተው ፔንትኮስታሎች የቤተ ክርስቲያን ሥልጣንና የመዋቅር አስፈላጊነት፣ እና የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የምታምነው የነበረው የሥልጣን እርከን አሳንሰው ወይም አናንቀው ለማየት አለመፈለጋቸውን ነው:: በፔንትኮስታሎች መካከል

194 Michael Harper, *The Holy Spirit Acts in the Church, Its Structures, Its Sacramentality, Its Worship and Sacraments," One In Christ* 12 (1976):322.
195 Lee, *Pneumatological Ecclesiology,* 16.
196 See Karkkainen, *Spiritus Ubi Vult Spiral: Pneumatology in Roman Catholic-Pentecstal Dialogue* (1972-1989) (Helinski, Finland: Luther-Agricola Society, 1998), 234-330.
197 See further Luigi Sartori, *The Structure of Juridical and Charismatic Power in the Christian Community," Concilium 109,* (New York: Seabury, 1978), 38-55.

ም በሁሉም ነገር ሙሉ በሙሉ ስምምነት አልነበረም:: ለምሳሌ:- የቤተክርስቲያን መዋቅር እና የቤተ ክርስቲያን ድርጅታዊ አሠራር ላይ አንድ ዓይነት አመለካከት ስላልነበረ በጉባዔ ከሚመራ (Congregational) እስከ ኤፒስኮፓል የሚደርስ የሐሳብ ልዩነት ነበር::[198] ለፔንትኮስታሎች "የቤተ ክርስቲያን" እውነተኛ ገፅታ የሚያሳይ አንድ ነጠላ የሆነ መለኪያ የለም::[199] የፔንትኮስታል ሙቭመንት አመለካከት "አዲስ ኪዳን አንድ ወጥ የሆነ የቤተ ክርስቲያን መዋቅር ሳይሆን፣ የተለያዩ መዋቅሮችን ነው የሚያሳየን::" የሚለው የጸና እምነት ነው::[200]

<u>የፔንትኮስታልና የካሪዝማቲክ ሙቭመንትን የጋራ የሆነ የሚመሳስሉባቸው ነገሮች ቢኖሩም፣ ልዩነት እንዳላቸው መግለፁ በጣም አስፈላጊ ነው:: ምክኒያቱም የካሪዝማቲክ ሙቭመንት ከተነሡበት ቤተ ክርስቲያን ይዘውት የመጡት ባህሎች እንዳሉ ማወቅ ይገባናል::</u>[201] ለምሳሌ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የካርዝማቲክ ሙቭመንት የተቀረፀው አንድም ለካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ባላቸው መሰጠት እና አንድም ደግሞ ለመንፈሳዊ ልምምድ ካላቸው መሰጠት ነው::[202]

<u>የፔንትኮስታል ሙቭመንት በመንፈሳዊ መነቃቃትና ዕድሳት ላይ ያተኰረ ስለሆነ በቤተ ክርስቲያን ታሪክና ባህል አያተኩርም::</u> <u>በአንፃሩ የካሪዝማቲክ ሙቭመንት ያለው ሥነ መለኮት ግን በቤተ ክርስቲያን ታሪክና በቀድሞ ዘመን የነበረው የቤተ ክርስቲያን አባቶች ባህል ላይ ያተኩራል::</u> በተጨማሪም የካሪዝማቲክ ሙቭመንት ከፔንትኮስታል ሙቭመንት ይልቅ በሕብረተ ሰብ ላይ ያተኩራሉ:: የመንፈስ ቅዱስ ልምምድም ከቤተ ክርስቲያን ባህል ለይተው አያዩትም:: እንዲያውም መንፈሳዊ ልምምዶች ከሰባቱ ቅዱስ ሥርዓቶች ጋር የሚያያይዙ እንደሆኑ ያምናሉ::

---

198 Harper, *"The holy Spirit,"* 324.

199 "Final Report of the Dialogue between the Secretariat for Promoting Christian Unity of the Roman Catholic Church and Some Classical Petecostals," *Information Service* 55 (1984), 2-3, 84.

200 Ibid.

201 See Kilian McDonnell, ed. *Presence, Power, Praise: Document on the Charismatic Renewal,* 3vols., (Collegeville, MN: Liteurgical Press, 1980).

202 See further Francis A. Sullivan, *"Catholic Charismatic Renewal," in the Dictionary of Pentecostal and Charismatic Movements,* 110-125; McDonnell, *"Catholic Charismatic Renewal and Classical Pentecostalism: Growth and Critique of A Systematic Suspicion," One In Christ*, 23 (1987): 36-61; McDonnell, ed. *The Holy Spirit and Power: The Catholic Charismatic Renewal*, (Garden City, N.Y.: Doubleday, 1975); McDonnell, *Charimatic Renewal and Churches*, (New York: Seabury, 1976); McDonnell, *Charismatic Renewal and Ecumenism*, (New York: Paulist, 1978).

ሌላው ደግሞ የካሪዝማቲክ ሙቭመንት የመንፈስ ቅዱስ ልምምዱን በባህል ካላቸው ሥነ መለኮት ጋር እያይዘው ያዩታል እንጂ፤ በተናጠል ይዘውት ከመጡት ባህላዊ አሠራር ጋር የሚጋጭ ወይም የሚቃረን አድርገው ሊያዩት አይፈልጉም።[203]

የምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን (በኋላ ወደ አንግሊካን ቤተ ክርስቲያን የለወጠው) ሚካኤል ሐርፐር የፔንትኮስታልና የካሪዝማቲክ ሙቭመንቶች ያደረጉት አስተዋፅዖ በሚከተሉት ነገሮች አጠቃሎታል።

"(1) የመንፈስ ቅዱስ ሚና ለግለሰቡ ሕይወትንና ኃይልን በመስጠት፤ በግለሰቡ በኩል ደግሞ ለቤተ ክርስቲያንና ለዓለም ይህንኑ ለማስተላለፍ መጠቀሙ፤

(2) በጠቅላላ የአማኞች ሕብረት በሙሉ በአምልኮም ይሁን፤ በቅዱስ ሥርዓቶች መሳተፉ፤

(3) "ለአገልግሎት ያልተለየው ሕዝብ" (Laity) በቤተ ክርስቲያን ሕይወትም ይሁን አገልግሎት በሙላት መሳተፍ፤

(4) የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለእግዚአብሔር ሕዝብ መሰብሰቢያና ክርስቶስ ለዓለም ሁሉ ያለውን ዓላማ መግለጫና ማሰራጨቷ አስፈላጊነት፤

(5) የእግዚአብሔርን ድንቅ አሠራር ለመግለጥ ሁኔታ ማመቻቸትና ልምምዱም እውን እንዲሆን መሆኑ፤

(6) የሐዋርያት መንፈስና ፀጋ የማገልገል እውነታ እንዲከሰት መፍቀድ፤

(7) የፔንትኮስታል ሙቭመንት በራስ የመምራትና የማስተዳደር መመሪያ በተለይም በሦስተኛው ዓለም ማበርታቱ።"[204]

## ሐ. የክርስቶስ አካልና የብልቶች አሠራር:-

(1ቆሮንቶስ 12:4-31፥ ሮሜ 12:3-8)

### 1. ትርጉመ ወሰን :-

#### 1.1 "የክርስቶስ አካል" ("THE BODY OF CHRIST")

*"እናንተም የክርስቶስ አካል ናችሁ፤ እያንዳንዳችሁም ብልቶች ናችሁ።"*

(1ቆሮ. 12:27)

---

[203] Congar, *I Believe In The holy Spirit*, especially 2: 165-169.

[204] Harper, *"Holy Spirit Acts,"* 323.

"የክርስቶስ አካል" የሚለው ሐሳብ "ቤተ ክርስቲያንን" ወይንም "የአማኞች ሕብረትን" ወይንም ከአይሁድና ከአህዛብ በክርስቶስ አምኖ የዳነው አዲሱ የክርስቶስ ሕብረተ ሰብን (ኤፌ. 2:11-22) ማለት ነው::[205] ሐዋርያው ጳውሎስ "የክርስቶስ አካል" የሚለው ሐሳብ ለምሳሌ በቆላስይስ 1:18 ላይ "*እርሱም (ማለትም ክርስቶስ) የአካሉ፤ ማለት የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው::*" በሚልበት ጊዜ ክርስቶስንና ቤተ ክርስቲያንን አንድ ወይንም እኩል ማድረጉ አይደለም:: ስለዚህም አካሉ ክርስቶስ አይደለም:: ክርስቶስም አካሉ አይደለም:: ይልቁንም ክርስቶስ የአካሉ (ማለትም የቤተ ክርስቲያን) ራስ ነው:: (ቆላ. 2:18፤ ኤፌ. 1:11-22) "እርሱም የአካሉ ማለት የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው::" (ቆላ. 1:18) በሚልበት ጊዜ የክርስቶስን የበላይነት እና ለቤተ ክርስቲያን መኖር፥ ቀጣይነትና፥ ተስፋ፥ ምክኒያት ክርስቶስ ኢየሱስ እንደሆነ የሚያመለክት ነው!!! (CHRIST IS ABOVE AND BEYOND THE CHURCH !!!) ከሐሰት አሠራሮችም ሆነ ትምህርቶች የሚጠብቃትም እርሱ ነው:: በእውነትና በፍቅርም የቤተ ክርስቲያን ማለትም የአካሉን አንድነት የሚጠብቅም እርሱ ነው!!! ቤተክርስቲያን (ማለትም የክርስቶስ አካል) የክርስቶስ ጌትነትና ሉዓላዊነት መግለጫ፤ ማስተላለፊያ፤ እና ማሰራጫ አሸንዳ ናት!!!

**1.2 "ቤተ ክርስቲያን" ("EKKLESIA")**

"*በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥*" (ማቴ. 16: 18)

"ቤተ ክርስቲያን" ቤተ ክርስቲያን መሆኗን የሚያስረግጡ ዋና ቁልፍ ነገሮች እንዳሉ በምዕራፍ ሁለት ላይ ጠቅሻለሁ:: "ቤተ ክርስቲያን" ከአይሁድና ከአሕዛብ የወጡና በክርስቶስ የዳኑ አዲስ ሕብረተ ሰብ ከመሆኗም ሌላ፥ "አንድነትን፥ ቅድስናን፥ እርቅንና፥ ወንጌልን፥ ማለትም የክርስቶስን ማንነት በሚያንፀባርቅ መልኩ የምሥራቹን የምታውጅ ናት::"[206] የቤተ ክርስቲያን አንድነት የሚጠበቀው በተመሳይነት ሳይሆን፥ አንድነት በልዩነት ውስጥ፥ ልዩነት ደግሞ በአንድነት ውስጥ በመጠበቅ ነው:: (1ቆሮ. 12:12፥14፥27፤ ሮሜ 12:3-8፤ ኤፌ. 4:1-13) ክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ በሠራው ፍፁም የማዳን ሥራ ምክኒያት ምንም እንኳን በእግዚአብሔር ፊት "ቅዱሳን" ተብለን ልንጠራ ብንችልም (POSITIONALLY)፤ በኑሮ ልምምድ (EXPERIENCIALLY) ግን ገና ተሰርተን ስላላለቅን "ለቅድስና" ተጠርተናል::

---

205 Colin Brown, ed., *NIDNTT*, vol. 1, 237-238.
206 See Charles Van Engen, *God's Missionary People*, 1991; Gerhard Kittel, ed. Trans. Geoffrey W. Bromiley, Vol. III, 518-526.

(ሮሜ 1:7፤ 1ቆሮ. 1:2) ቅድስናዋን ያልጠበቀች ቤተ ክርስቲያን "ቤተ ክርስቲያን" ንች ለማለት ያስቸግራል:: ሌላው የቤተ ክርስቲያን ባህሪ የምትሰብከው ወንጌል የእርቅ ወንጌል ስለሆነ፥ (2ቆሮ. 5:16-21) የምትሰብከውን የምትኖር፥ የምትኖረው ንም የምትሰብክ ልትሆን ይገባል:: በመሪዎቿና በአገልጋዮቿ መካከልም ይሁን፥ በምዕመኗ መካከል (በመሪዎች ምሳሌነት) ይቅርታና እርቅ መለማመዷን ልታረጋግ ጥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይጠበቅባታል:: የቤተ ክርስቲያንን ማንነት የሚገልጠው ሌላው ነገር በቃልም ይሁን በሥራ የምሥራች የሆነውን ወንጌል ("እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው"- ሮሜ 1:1-4) ልትሰብክና ልታውጅ ይገባል::

**2. የክርስቶስ አካልና የብልቶች አሠራር:-** (1**ቆሮ.** 12: 4-31)

*"የጸጋ ስጦታ ልዩ ልዩ ነው፥ መንፈስ ግን አንድ ነው፤ አገልግሎትም ልዩ ልዩ ነው፥ ጌታም አንድ ነው፤ አሠራርም ልዩ ልዩ ነው፥ ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው::"* (1ቆሮ. 12:4-6)

**2.1 ቁጥር 4-6:-**

የክርስቶስ አካልና የብልቶች አሠራር (የቤተ ክርስቲያን አሠራር) ለመዳሰስ በምናስብበት ጊዜ በማስተዋል ልንመለከተው ይገባል ብዬ አምናለሁ:: <u>የጸጋ ስጦታ፥ አገልግሎት፥ እና አሠራር ልዩ ልዩ ነው::</u> <u>በእነዚህ ውስጥ አልፎ የሚሠራው እግዚአ ብሔር አብ፥ እግዚአብሔር ወልድና፥ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግን አንድ አም ላክ ነው::</u> በአንድነት ውስጥ ልዩነትን፥ በልዩነትም ውስጥ አንድነትን ጠብቆ ለዘላለ ምና ለዘመናት የሚኖረውን የሥላሴዎች የአሠራር ሞዴል በመከተል የጸጋ ስጦታን ፥ አገልግሎትንና፥ አሠራርን ልናከናውን፥ የክርስቶስን አካል አንድነት ለመጠበቅ ያስችለናል::

<u>የሥላሴን አሠራር በምናይበት ጊዜ አንዱ በሌላው ላይ ትጽዕኖ ሳይኖረው፥ አንዱ ከሌላው ጋር ሳይቃረን፥ አንዱ በሌላው ሳይሰለጥን፤ አንዱ ለሌላው ግርዶሽ ሳይሆንበት ፍጹምና ምሉዕ በሆነ አንድነት በልዩነት ውስጥ፤ ልዩነትም በአንድነት ውስጥ እየገለጹ እንደ ውሃ አብረው ይፈሳሉ:: የአንዱ ክብር የሌላው ክብር፥ የአንዱ ዓላማ የሌላው ዓላማ፤ የአንዱ ሽክም የሌላው ሽክም ነው!!!</u>

ሐዋርያው ጳውሎስ "አካል አንድ እንደሆነ፥ ብዙም ብልቶች እንዳሉበት፥ ነገር ግን የአካል ብልቶች ሁሉ ነው" ይላል:: (1ቆሮ. 12:12) ስለዚህም ነው የሥላሴን ምሳሌነትና ሞዴል በመከተል በክርስቶስ አካል (ማለትም በቤተ ክርስቲያን) ውስጥ

የጸጋ ስጦታዎችን፥ አገልግሎትን፥ እና አሠራርን በምንለማመድበት ጊዜ የአካሉ አንድነትና መታነጽ በማሰብ ልናደርጋቸው ይገባል። በአንድ በኩል የጸጋ ስጦታዎች ልምምድ (አጠቃቀም) (1ቆሮ. 12)፥ በሌላ በኩል የአስተዳደር ኃላፊነት (1ቆሮ. 14) መደረግ ያለባቸው የክርስቶስን አካል (ማለት ቤተ ክርስቲያንን) ለማነጽ፥ ለማሳደግና ለማጐልበት በፍቅር (1ቆሮ. 13) መሆን አለበት። ይህም ከልብ የሆነና በጌታም ፊት ተፈትኖ የወጣ ፍጹም ትሕትናን የሚጠይቅና በብልቶችም መካከል መቀባበልን የሚጠይቅ ጉዳይ ነው!!!

የጸጋ ስጦታዎች አጠቃቀምም ይሁን የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በባሕሪያቸው ክፋትን አመፅንና ትዕቢትን የሚያካትቱ (የሚያስተናግዱ) አይደሉም። ትዕቢት ፥ ክፋትና አመፅ ባለበት ሥፍራ የክርስቶስ አካል ከሚታነጽ ይልቅ ይናጋል፤ ይታወካል፤ ከሚያድግ ይልቅ ይቀጭጫል፥ ከሚጐለብት ይልቅ ምንም ነገር ለማድረግ ኃይል ያጣል። ከዚህም በላይ የጌታ ኢየሱስን ባሕርይ ስለማያንፀባርቅ አስተዋይ ለሆነ ሰው ልብ ይሰብራል። <u>የእግዚአብሔርን ልብ የሰበረ ነገር ልባችንን ካልሰበረ ራሳችንንልንመረምር ይገባል ብዬ እሰባለሁ</u>!!! በውጭ ላሉት ለማያምኑት ሰዎችም ያልሆነ ስዕል በመስጠት ስለ ቤተ ክርስቲያን የነበራቸውን አጠባበቅ ስለሚያበላሽ ወንጌልን እንዳይሰሙና እንዳይቀበሉ መሰናክል ይሆንባቸዋል።

2:2 **ቁጥር** 14-30 ፦

ሐዋርያው ጳውሎስ በአካሉ ውስጥ ያሉት ብልቶች "ብዙዎች ናቸው" ካለ በኋላ፥ ለናሙና ያህል ሦስት የብልት ዓይነቶች ገልጿል። እነዚህ የብልት ዓይነቶች በይሁዳ ፥ በሰማርያና በገሊላ አውራጃዎች የነበረውን ሕዝብ ባሕርይ የሚያንፀባርቁ ናቸው።

- አንደኛ፥ "የሰማርያ ሰዎች መንፈስ" (1**ቆሮ**. 12፥ 14-20) ፦

እነዚህ ብልቶች የተሰጣቸውን ስጦታ ማክበር የተሳናቸው፥ የሰጪውንም ባሕርይ ካለመረዳታቸው የተነሣ የሚያጉረመርሙ፥ የማያቋርጥ የውድድርና የፉክክር መንፈስ ያላቸው፥ ሌላው ብልት የሆነውን ካልሆኑ፥ ሌላው ብልት ያለው ከሌላቸ በስተቀር የማይረኩና እረፍት የሌላቸው የብልት ዓይነት ናቸው። ይህ ባሕርያቸው <u>የበታችነት ስሜት</u> እንዲሰማቸውና አጉል የሆነ መፈሳዊነት የጎደለው "መሳይ ትሕትና" እንዲለማመዱ ስለሚያስገድዳቸው ሳያውቁት ሌላ የትዕቢት ገጽታ ያንጸባርቃሉ። የተሰጣቸውንም ጸጋ ማክበር ስለሚሳናቸው ሌሎች ሰዎች ጸጋቸውን እንዳይጠቀሙበት ያግዳሉ። ራሳቸውንም በማያቋርጥ "የሌላውን ጸጋ የሚቋምጥ ሕይወት" እንዲኖሩ ስለሚያደርጋቸው ምንም ዓይነት እርካታና ዕረፍት የሌለው ሰው ይሆናሉ።

የሰማርያ አውራጃ ሕዝብ ምንም እንኳን ከጅማሬአቸው አይሁዶች ቢሆኑም በነ ኅምያ ዘመን ከነበሩት ከጦቢያና ከሰንባላጥ ጀምሮ ከይሁዳ ሕዝብ ጋር ከነበራቸው ፉክክርና ውድድር የተነሣ ራሳቸውን ከአሕዛብ ጋር ያዳቀሉ ሰዎች ናቸው:: በይሁዳ ሕዝብም ላይ ከማመፃቸው የተነሣ÷ እግዚአብሔር የመረጣትን የእስራኤል ዋና ከተ ማ ኢየሩሳሌም የነበረውን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ትተው፤ በሰማርያ ሌላ የጣዖታት ቤተ መቅደስን፤ የእግዚአብሔርን ነቢያት ንቀው÷ የራሳቸው ነቢያትን አበጁ:: በኋለኛው ዘመንም በነህምያና በዘሩባቤል፤ በካህናቱም በዕዝራና በኢያሱ የተ ጀመረውን ሥራ በፅኑ ከመቃወማቸውና ከማስተጓጎላቸውም ሌላ፤ ነህምያንም ለመግ ደል ብዙ ጥረት ሲያደርጉ እናያቸዋለን:: ከዚህ የተነሣ እግዚአብሔር በሰማርያ አው ራጃ ውስጥ የፈፀማቸው ተአምራቶች በጣም ጥቂቶች ናቸው::

(2ነገ. 2÷ 19-22፤ 23-25፤ 7÷ 1-20) የሰማርያ ሕዝብ ከእንዲህ ዓይነት መንፈሳዊ ዝቅጠት የወጣው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሳምራዊቷን ሴት ሕይወት ከለወጠ በኋላና÷ በእርሷም ምክኒያት ለሰማርያ ሕዝብ ከተገለጠ በኋላ ነው::

(ዮሐ. 4÷ 1-42)

❖ ሁለተኛ÷ "የይሁዳ አውራጃ ሕዝብ መንፈስ" (1ቆሮ. 12÷ 21) :-

እነዚህ የብልቶች ዓይነት የአካሉ ብልት መሆናቸው አንሷቸው ብቻቸውን "አካ ል" ለመሆን የሚመኙ ናቸው:: ካለ እነርሱ በስተቀር ሌሎች ብልቶች እንዳሉ ለማሰ ብም ይሁን÷ ለማስተናገድ የማይችሉ÷ የአካሉ ራስ ለመሆን ስለሚፈልጉም ሳያውቁ ት የጌታን ሥፍራ ለመውሰድ ሲቋምጡ ዘመናቸው ያልፋል:: የክርስቶስ አካል የሚ ቆመው በእነርሱ የጸጋ ስጦታ ብቻ ይመስላቸዋል:: በውስጣቸው ከበቀለው ስውርም ይሁን ግልጥ ትዕቢት የተነሣ <u>የበላይነት ስሜት</u> የሚያጠቃቸው ናቸው:: ይህ ባሕሪያ ቸው የሌሎችን ሰዎች የጸጋ ስጦታ እንዲያናንቁና እንዲጋፉ ስለሚያደርጋቸው÷ ከሌሎች ሰዎች ጋር ተጣጥመው በመቀናጀት ማገልገል ይሁን መገልገል አይፈልጉ ም:: ከዚህ ይልቅ "የሁሉ ነገር ማዕከል" እንደሆኑ ስለሚያስቡ የሥልጣንና የኃይል ጥያቄ በጣም የሚያሳስባቸው ናቸው:: ሌላው ሕዝብ ሁሉ የሚያመልከው ሰው ለመሆን ከመፈለግም ወደ ኋላ የማይሉ ናቸው::

የይሁዳ አውራጃ ሰዎች ራሳቸውን ከሰማርያና ከገሊላ አውራጃዎች የበለጠ የበ ላይ አድርገው ይመለከቱ ነበር:: ለዚህ ትዕቢታቸው መነሻና ምክኒያት የሆኑ ሦስት ዋና ነገሮች ነበሩ:: እነዚህም የሚከተሉት ናቸው:-

- ✓ <u>አንደኛ በሃይማኖት አንፃር</u>፦ ሁሉም የሃይማኖት አባቶች፣ ማለትም ፈሪሳውያን ፥ ጸሐፍትና ሰዱቃውያን የተነሡት ከይሁዳ አውራጃ ነው:: አብዛኛዎቹ የእግዚ አብሔር ነቢያት የተነሡትም ከይሁዳ አውራጃ ነው:: (ዮሐ. 1፡47) እውነተኛ የእግዚአብሔር ነቢይ ከሌላ አውራጃ አይጠበቅም ነበር:: የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስም በዚሁ አውራጃ በኢየሩሳሌም ውስጥ ነው የነበረ ው::
- ✓ <u>ሁለተኛ በኢኮኖሚ አንፃር</u>፦ በእስራኤል ምድር ሀብታሞችና ባለጠጎች የትነበሩ ቢባል በይሁዳ አውራጃ ነው:: እንዲያውም ጌታ ኢየሱስ በምድር በተመላለሰበ ት ዘመን ከሮም ቀጥሎ በዓለም ሁለተኛው ትልቁ ባንክ የነበረው በኢየሩሳሌም፥ ያውም በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውስጥ ነበር:: (ዮሐ. 2፡13-17፣ ማቴ. 21 ፡12-13፣ ማር. 11፡15-16፣ ሉቃስ 19፡45-46)
- ✓ <u>ሦስተኛ በፖለቲካ አንፃር</u>፦ ከሮማውያን ቀጥሎ የእስራኤልን ሕዝብ አንቀጥቅጠ ው ይገዙ የነበሩት ሰዱቃውያን ከይሁዳ አውራጃ የተነሡ ናቸው:: ስለዚህም በፖለቲካው አኳያም የበላይነት ነበራቸው::

◆ **ሦስተኛ፥ "የገሊላ አውራጃ ሕዝብ መንፈስ" (1ቆሮ. 12፥ 22-25) ፦**

ሐዋርያው ጳውሎስ እነዚህን ብልቶች ሲገልፃቸው "ነገር ግን ደካሞች የሚመስ ሉ የአካል ብልቶች.." (ቁ. 22)፥ "ከአካል ብልቶችም ያልከበሩ ሆነው የሚመስሉን ..." (ቁ. 23)፥ "በምናፍርባቸውም ብልቶቻችን..." (ቁ. 23) ይላቸዋል:: ይህን "ደካ ሞች፥ ያልከበሩ፥ የምናፍርባቸው ብልቶች" የሚለውን መግለጫ ከተጠቀመ በኋላ በመቀጠልም "ይልቁንም የሚያስፈልጉ ናቸው፣...በሚበዛ ክብር እናለብሳቸዋለን፣... ክብር ይጨመርላቸዋል::" የሚሉ ጉዳዮችም ጠቅሷል:: እነዚህ የብልቶች ዓይነት ከድካማቸውና ያልከበሩና የሚያሳፍሩ መምሰላቸው ካላቸው እውቀት በስተቀር ስለ ራሳቸው ሌላ የሚያውቁት የላቸውም:: በአንድ በኩል የተሰጣቸውን ጸጋ ማቃለል፣ በስጢውም ላይ ማጉረምረም፣ የሌሎችን ሰዎች የጸጋ ስጦታ አይተው መቋመጥ፥ መቅናት በግል ምኞት መወጠር አይፈልጉም:: በሌላ በኩል ደግሞ በትዕቢት ምክኒያ ት ስለ ራሳቸው ያላቸውን ግምት ከሚገባ በላይ በመወጠርም በሌሎች ሰዎች ላይ ለመሰልጠን፣ ሥልጣንና ኃይል በእነርሱ ዙሪያ እንዲሽከረከርም "አካል" የመሆን ፍላጎት፥ በራሳቸው ተመክተውም የሌላውን ሰው ጸጋ መጋፋትም አያውቁበትም::

የገሊላ አውራጃ ሰዎች የበላይነት ስሜትም ይሁን፥ የበታችነት ስሜት የሌላቸ ው <u>ያልተወሳሰቡና ቅንነት ሰዎች</u> ናቸው:: የእነርሱ መለያ "ያልተወሳሰበ ኑሮ" ነው::

በሐዋርያት ሥራ 4:13 ላይ "...መጽሐፍን የማያውቁና ያልተማሩ ሰዎች እንደሆኑ አስተውለው አደነቁ፥ ከኢየሱስም ጋር እንደነበሩ አወቁአቸው፤" እንዳለው አሣ ከማጥመድ ሌላ፣ በጊዜው በነበሩት የምኩራብ ትምህርት ቤት ገብተው መደበኛ ትምህርት ያልተማሩ (የሐዋ. ሥራ 4፥ 13) ሰዎች ናቸው:: ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ የነበረው ምድራዊ አገልግሎት እየሰፋ በመምጣቱ ምክኒያት የራሱን ደቀ መዛሙርት እንዲኖሩት ስለፈለገ ሌሊቱን በሙሉ ሲፀልይ አደረ:: (ማር. 3:13-19፣ ማቴ. 10:1፣ ሉቃስ 6:12-16) ጌታ ኢየሱስ "*በነዚህም ወራት ይፀልይ ዘንድ ወደ ተራራ ወጣ፤ ሌሊቱንም ሁሉ ወደ እግዚአብሔር አብ ሲጸልይ አደረ:: በነጋም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን ጠራ፥ ከእነርሱም አሥራ ሁለት መረጠ፥ ደግሞም ሐዋርያት ብሎ ሰየማቸው፤ ...*" (ሉቃስ 6: 12-13) በዚህ ጊዜ ያደረገው የጥሪ ምርጫ አስደናቂ እንደሆነ ለአንባቢዎቼ ለመግለጽ እፈልጋለሁ::

ይኸውም የበታችነት ስሜት ከነበራቸው የሰማርያ ሕዝብ መካከል አንድም ደቀ መዝሙር በአሥራ ሁለቱ መካከል አናይም፣ የበላይነት ስሜት ይሰማቸው ከነበሩት የይሁዳ ሕዝብ መካከል የመረጠው አንድ ደቀ መዝሙር፥ ያውም ጌታን አሳልፎ የሰጠው አስቆረቱ ይሁዳን ነው:: አሥራ አንዱን ደቀ መዛሙርት የመረጠው "ያልተወሳሰበ ኑሮ" (SIMPLICITY) ከነበራቸው ከገሊላ አውራጃ ነው!!! (የሐዋ. ሥራ 1: 11፥ 2: 7፥ 3: 6፥ 4: 13፥ 5: 41-42) ጌታም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንዲሞሉ ካደረገ በኋላና አብሮአቸውም ሲሠራ፥ "አንዱ ሰላሣ፥ አንዱ ስድሳ፥ አንዱም መቶ አፈራ፤" እንደ ተባለ፥ ፍሬአቸውን እጅግ ባረከ:: በወንጌልም ዓለምን ገለበጡ:: ከኢየሩሳሌም ጀምረው ወንጌልን የዓለም ዋና መናኸሪያ (SUPER POWER) የነበረችውን አገር እስከ ሮም ድረስ አደረሱ!!!

ይህን ሐሳብ ለማጠቃለል በክርስቶስ አካል ውስጥ የመጀመሪያውና የሁለተኛው የብልቶች ዓይነት መንፈስ በሚኖርበት ጊዜ አይ-አዎን ኑሮ መኖር እንጀምራለን:: በአንድ በኩል ሌላው ብልት ደስ ሲለው አብሮ ደስ ከመሰኘትና ክብሩን ከመካፈል ይልቅ፥ ብስለት የሌለው ባሕርይ በማሳየት ማዘን፥ መቅናትና፥ መቆጨት እንጀምራለን:: በሌላ በኩል ደግሞ ሌላው ብልት ሲሰቃይ አብረን መቃተት ሲኖርብን፤ በመሰቃየቱ ደስ ይለናል:: የእግዚአብሔር ልብ የሚያርፈው የበታችነት ወይም የበላይነት ስሜት ባላቸው ሰዎች ሳይሆን፤ ያልተወሳሰበ ሕይወት (SIMPLICITY) ባላቸው ሰዎች ነው!!! ሐዋርያው ጳውሎስ "ደግሞም ከሁሉ የሚበልጥ መንገድ አሳያችኋለሁ" (1ቆሮ. 12:31) ካለ በኋላ የነገር ሁሉ መሠረት ፍቅር እንደሆነ በ1ቆሮንቶስ

13:1- 13 ላይ ገልፆታል። እንዲያውም በምዕራፍ 14፡ 1 ላይ ደግሞ:-"ፍቅርን ተከታተሉ" ይላል።


***የክርስቶስ አካል (ቤተ ክርስቲያን) እያደገ፥ እየጐለበተና፥ እየሰፋ እንዲመጣ ከተፈለገ የሚከተሉትን ነገሮች መገንዘብ ይኖርብናል:-***

- የአካል ብልቶች ሁሉ ተሳትፎ፥ የቤተ ክርስቲያንን አመራር ያጐለብተዋል እን ጂ አያቀጭጨውም። በክርስቶስ አምነው በዳኑት ሰዎች (በአማኞች) ውስጥ እምቅ ችሎታ እና ጸጋ አለ። ይህንን እምቅ ችሎታና ስጦታ ፈልቅቆ የማውጣት ሥራና እንዲለማመዱትም የማበረታታት ኃላፊነት የፓስተሮችና የቤተ ክርስቲ ያን መሪዎች ሁሉ ነው። (ሮሜ 12፡ 4-8፥፤ 1ቆሮ. 12፡ 3-8፤ ኤፌ. 4፡ 11-13)
- የክርስቶስ አካል (ቤተ ክርስቲያን) አንድነት የሚጠብቀው ልዩነታችንን ስንቀበ ልና አንዱ የሌላውን ጸጋ ሲቀበል፥ ሲያከብርና፥ ሲጠቀም ብቻ ነው። የአንድነ ታችን ውበት በልዩነታችን ውስጥ የሆነውን ያክል፤ ደግሞም ሐዋርያው ጳውሎ ስ "*በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ*" (ኤፌ. 4፡ 3) እንዳለ ው በልዩነታችን ውስጥ የክርስቶስ አካልን (የቤተ ክርስቲያንን) አንድነት ልንጠ ብቅ ይገባል።
- በክርስቶስ አካል (በቤተ ክርስቲያን) ውስጥ ያሉት አራት ቢሮዎች (ኤፌ. 4፡ 1 1)፥ የሽምግልና፥ የድቁና፥ የአስተዳደር፤ እና ሌሎች የአገልግሎት የጸጋ ስጦታ ዎች ለአካሉ ሲባል ለአሠራር እንዲመች ከጌታ የተሰጡን እንጂ፤ የሥልጣንና የኃይል ጥያቄ እንዲመልሱልን አይደለም!!! (ቆላ. 1:25፤ 2ቆሮ10:8፤ 2ቆሮ. 13 :10) ስለዚህም ነው "በክርስቶስ አካል ውስጥ ማንነው የበላይ?" የሚለው ጥያቄ በራሱ የሞተ ሐሳብ የሚሆነው። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳለው "ብቃታችን ከእ ግዚአብሔር ነው እንጂ በገዛ እኛችን እንደሚሆንአንዳችን እንኳ ልናስብ እራሳ ችን የበቃን አይደለንም።"(2ቆሮ. 3፡ 5)
- ኬቪን ጋይስ የሚባለው ጸሐፊ በመጽሐፉ ውስጥ ስለ ሥላሴ ምስጢር ለመግለጽ እንዲያመቸው ያቀረበውን ስዕላዊ መግለጫ እኔ ደግሞ የክርስቶስ አካል አሠራ ርን ለማሳየት ከዚህ በታች ተጠቅሜበታለሁ።[207]


[207] Kevin Giles, *The Trinity and Subordinationism - The Doctrine of God & The contemporary Gender Debate*, (Downers Grove, IL: InterVaristy Press, 2002), 118-121.

### መ. የቤተ ክርስቲያን የሥልጣን እርከንና መዋቅር?
### ወይንስ ገደብ የሌለው ፍቅርና የጸጋ ቅብብሎሽ?


1. የሥልጣን እርከንና መዋቅር ላይ ያተኰረ ቤተ ክርስቲያን፡-
**(THE HIERARCHIACHL MODEL)**




2. "የአባትነት / የአውራነት ሥልጣን" ያለበት ቤተ ክርስቲያን ፡-
**(THE MONARCHIACAL MODEL)**




3. **ፓስተሩና የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች**
**በምዕመን ላይ ሥልጣናቸውን የሚገልፁበት ቤተ ክርስቲያን**
**(THE FILIOQUE MODEL)**





4. **በአንድ ልብና በአንድ ሐሳብ አብረው የሚፈሱ መሪዎች ያሉበት ቤተ ክርስቲያን (THE SYMMETRICAL MODEL)**

**4.1**



4.2




4.3

